# የመምህሩ መምሪያ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ደረጃ 3 እና 4

ሥርዓተ ትምህርት ለ

ለ1 –ለ 6

www.besweb.com

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊ አገልግሎቶች

በእንግሊዝ የበጎ አድራጎት ምዝገባ (ቁጥር 1096157)

### የተልዕኮ መልእክት

የአሁኑንና መጪውን ትውልድ በእግዚአብሔር ቃል ለመድረስ ለዓለም አቀፋዊ ግልጋሎት የሚውሉ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለእርስዎ በማዘጋጀት እርስዎም ሌሎችንም እንዲያገለግሉ ለማድረግ ነው።

### የራእይ መልእክት

የዓለም ቋንቋዎችን በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች በመጠቀም በእኛ ማዕከላዊ እሴቶች መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊ መረጃዎችን ከእኛ ጋር ለሚሠሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

## ጠቅላላ መረጃ

**የመጽሐፍ ቅዱስ የትምህርት አገልግሎት ምን እንደሚያከናውን:-**

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትምህርት አገልግሎት (ቢኢኤስ) በኢንግሊዚኛ የተዘጋጁ። የአዲስ ህይወትን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ሰብስቦ በማሣተም፤ በፖስታ ቤት በኩል የሚሠጡ ትምህርቶችንና ሌሎች ተመሣሣይ በእንግሊዝ እንዲሁም በሌሎች አገሮች የሚሠሩ ድርጅቶችን በቢኢኤስ በኩል በመጎብኘት፤ በማስተሣሠር፤ በማስተዋወቅና በማሠልጠን ይረዳል። ከዚህ በተጨማሪም ቢኢኤስ በአሁኑ ወቅት በሌሎች አገሮች ውስጥ ትምህርቶችን በመተርጎም፤ በመንደፍ፤ በማሣተምና በማሠራጨት ሥራ ላይ ከተሠማሩ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሠራል። ትምህርቶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች በነፃ የሚሠጡ ሲሆን ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ተጀመረ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አገልግሎት አዘጋጆች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት በኢንግሊዚኛና በሌሎች ቋንቋዎች ለሚዘጋጁ ትምህርቶች ኃላፊነት አለባቸው። ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት

የሚዘጋጁ ትምህርቶች የሚታተሙት በA4 ፎርማት (አቀራረብ) ሲሆን ይህም በሌሎች አከባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በየአራት ሣምንቱ ፈተናው ወደ ሚታረምበት የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል ለመላክ እንዲያመች ነው። በአሁኑ ጊዜም ለእያንዳንዱ ቤት የወንጌል ሥርጭት መነቃቂያዎች ምስጋና ይግባውና በቤል ፋስት ውስጥ ለስድስት ወራት የሚያገለግል ትምህርት በA5 ፎርማት (አቀራረብ) ስለሚታተም በተለይም የፖስታ አገልግሎት በማይገኝባቸው አብያተ ቤተ ክርስቲያናትና ትምህርት ቤቶች ጉዳዩን በጣም እንዲቀላጠፍ አድርጎታል። ቢኢኤስ በባህሪይው የሚለየው የሚዘጋጁት ትምህርቶች የቤት ወይም የቡድን ጥናትን ያማከሉና ተማሪዎቹም ሥርዓተ ትምህርቱን እስከ 20 ዓመታት ድረስ በቤተ ክርስቲያን/ትምህርት ቤት ያለማቋረጥ እንዲከታተሉ ስለሚያደረግ ነው። ለተወሠኑ የዕድሜ ደረጃ ቡድኖች የሚያገለግሉ አምስት የትምህርት ደረጃዎች ያሉ ሲሆን እነርሱም የቅድመ-ትምህርት ቤት፤ ከ5-7፤ ከ8-10፤ ከ11-13ና ከ14-16 ናቸው። ለእያንዳንዱ ቡድን የሶስት ዓመታት ሥርዓተ ትምህርት ይዘጋጃል። በተመሣሣይ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የቡድን አባላት የተለያዩ ችሎታዎች ሊኖራቸው ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መረጃዎች ለልጆች የእግዚአብሔርን ቃል፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና በህይወታቸው የወንጌልን ጠቃሚነት ተግዳሮቶችን እንዲጋፈጡ እድል ይሠጣቸዋል።

በኢንግሊዚኛ ለትምህርት ተዘጋጅተው የታተሙ ቅጂዎች ከቢኢኤስ ድህረ ገጽ - www.besweb.com ወይም ከዓለም አቀፍ ጽህፈት ቤቱ ይገኛሉ። በድህረ ገጹ ላይ በሌሎች ቋንቋዎችም ይገኛሉ። ጽህፈት ቤቱ የቢኢኤስ ማዕከል ለማቋቋም የሚረዱ መረጃዎችን አለው።

## የቢኢኤስ መገኛ አድራሻዎች


**ዓለም አቀፋዊና የሠሜን አየርላንድ ፀሐፊ (ለትምህርት የተዘጋጁ ጽሁፎች በሙሉ)**
Mr S Balmer, 37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland. BT74 6AA
Phone: 0286 632 2462
Email: sam@besweb.com

**UK Secretary**
Mr Stephen Gillham, 32 Firs Glen Road, West Moors, Ferndown, Dorset BH22 0ED
Phone: 01202 873500
Email: stephen@sgilllham.co.uk

**ድህረ ገጽ:** www.besweb.com
**ኢሜል:** info@besweb.com

## ለአስተማሪዎች የሚያገለግሉ መመሪያዎች

በመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ይዘጋጁ የነበሩት በፖስታ ትምህርት ቤት ማዕከል በኩል ቢሆንም ትምህርቶቹ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ የዋሉት የፖስታ ቤት ሥርዓት አስተማማኝ ባልሆነባቸው ወይም በማይገኝባቸው በአፍሪካ፤ በህንድና በሌሎችም በታዎች በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ትምህርት ቤቶች ነበር። የማስተማሪያ መመሪያዎች የተዘጋጁት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት በጥቅም ላይ እንዲውሉ ነው። በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ እንዲያገለግል የተዘጋጀው የማስተማሪያ መመሪያ እድሜያቸው ከ11-16 ለሆኑ በደረጃ 3 እና 4 ለሚገኙ ተማሪዎች ነው። በእያንዳንዱ ሣምንት የሚሠጠው መመሪያ ተመሣሣይ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎችን ይጠቀማል። ስለሆነም የሚያዚያ ትምህርቶች የሚያተኩሩት በፋሲካ በዓል ላይ ሲሆን የታህሳሶቹ ደግሞ ትኩረታቸው በገና በዓል ላይ ነው።

አንዳንድ በታዎች በየሣምንቱ በA4 የሚዘጋጅ ትምህርት ሲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ ባለ A5 24 ትምህርቶችን የሚይዝ ትንሽ መጽሐፍ ይጠቀማሉ። ብዙውን ጊዜ አስተማሪው ወይም መሪው የየወሩን A4 ትምህርቶች ለተማሪዎቹ በቤተ ክርስቲያን ወይም ትምህርት ቤት ወይም ቤት ወርክ ሺቱን ሠርተው በሚቀጥለው ሣምንት እንዲያመጡት ያደርጋል። በወሩ መጨረሻ አስተማሪው ወይም መሪው ወርክ ሺቱ ላይ የተሠሩትን ትምህርቶች በመሠብሠብና በማረም በተሻለ ፍጥነት ተማሪዎቹ እንዲደርሳቸው ያደርጋል።

ትንንሽ መጽሐፍቱ በሥራ ላይ በሚውሉበት ወቅት በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ተሠብስበው ይታረማሉ። በብዙ አጋጣሚዎች እንደዚህ ማድረግ እንደማይሣካ እንገነዘባለን። ስለዚህ አስተማሪው ወይም መሪው የሚታረሙትን ትምህርቶች በክፍል ውስጥ በማሠራጨትና መልሶችን በመስራት ተማሪዎቹ የጓደኞቻቸውን አርመው ውጤት እንዲሠጡ ያደረጋል። በመጽሐፉቶቹ የመጨረሻ ገፆች ላይ የተማሪዎቹ ወርሃዊ የትምህርት ውጤት የሚቀመጥበትና የተማሪው የመሻሻል ሁኔታ አስተያየት የሚፃፍበት ባዶ በታ አለ። ተማሪው በስድስት ወራት ውስጥ ያስመዘገበውን ውጤት የሚያሣይ የምስክር ወረቀትም በየመጨረሻው ገጽ ተያይዟል።

## ለአስተማሪዎች የሚያስፈልግ ዝግጅት

በዚህ የማስተማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ መመሪያ ሠጪዎች በመሆን አስተማሪው የራሱን ሃሣብና ተነሣሽነት እንዲጠቀም ፈጽሞ ትዕዛዝ አንሠጥም። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ የምትጠቀምባቸው መመሪያዎች ናቸው።

- **ታሪኩን በሚገባ ተረዱ -** አስተማሪዎች በተቻለ መጠን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት ከሚሠጡ ትምህርቶች ጋር በሚገባ መለማመድ አለባቸው። በመሠረቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት በአስተማሪው መጠናቀቅ አለበት። ለእያንዳንዱ ትምህርት የሚዘጋጁ መመሪያዎች እንደ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ያገለግላሉ።

- **የምታስተምሩትን ትምህርት በሚገባ ተረዱ -** እያንዳንዱ የትምህርት እቅድ ከተጠናቀቀ በኋላ ።ይህንን እንማራለን። ከሚሉ ትዕዛዛት ባሻገር ልጆች የአስተማሪውን ትምህርት ከተከታተሉና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ያገኙትን ትምህርት ሲያጠናቅቁ ሁለት የትምህርቱ ግቦች መሣካታቸውን ማስተዋል ትችላላህ። የመጀመሪያው ሃሣብ የታሪኩን እውቀት የሚያስገነዝብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልጆች ስለ ታሪኩ እንዲያስቡ፤ ተግባራዊ እንዲያደርጉና ምላሽ እንዲሠጡ ያበረታታል። እነዚህ ሃሣቦች ከትምህርቱ የተገኙ ትክክለኛዎቹ የዋናው ጽንሰ ሃሣብ/እውነታ በመሆናቸው አስተማሪዎች እነዚህን በመማር ማስተማሩ ግምገማ ወቅት መጠቀም ይችላሉ።

- **አስተዋውቁ -** በሁሉም ትምህርቶች ልጆች ካሉበት ሁኔታ ልምምድ እንጀምራለን። በታሪኩ መጀመሪያ ልጆች እንዲወያዩበት ለማስቻል የተለያዩ መንገዶችን እንደ መግቢያ እንጠቁማለን።

- **አስተምሩ -** በታሪኩ ውስጥ ቁልፍ ነጥቦችን ሠጥተናል። አስተማሪው በሚያስተምርበት ወቅት የእነዚህን ቁልፍ ነጥቦች ሃሣብ በሚገባ ተረድቶ እንጂ ሲያስተምር እንደ ማጣቀሻ ሣይጠቀም በሚያስደስትና በሚስብ መልኩ ማስተማር አለበት። አስተማሪው ልጆቹ ከታሪኩ ዋናውን ትምህርት እንዲረዱለትና ከተማሩት ታሪክ የሚሠጡትን ምላሽ መረዳት ይፈልጋል። ተገቢ በሆነበት በታ ሁሉ ጥቂት ማብራሪያዎችን ከሚነገረው ታሪክ ጋር እንዲቀናጅ ለማድረግ ሞክረናል። እነዚህ ሁል ጊዜ በተለየ የአፃፃፍ ስልት /ኢታሊክስ ይቀመጣሉ።

- **አስጠኑ -** ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር የተያያዘ መሪ ጥቅስ አለ። በጥቂት አጋጣሚዎች ሁለት መሪ ጥቅሶች የተሠጡ ሲሆን ይህም ለልጆች ትምህርት በቀላሉ እንዲያገለግል ነው። ልጆች እነዚህን መሪ ጥቅሶች እንደሚማሯቸው ተስፋ ስለምናደርግ ሁል ጊዜ እያስታወሱ በመጽሐፍ ቅዱስ መሪ ጥቅሶች ላይ የተመሠረተ እውቀት እንዲገነቡ ማድረግ ነው።

- **አጠናቁ -** በትምህርት ቤት ውስጥ የልጆችን ችሎታ በሚያጠናቅቁት ዎርክ ሺትና የሚሠጡትን የአስተማሪው መርጃ መረዳት ይቻላል። ለጥቂቶች የሚያስፈልገው ነገር አስተማሪው የመማሪያ መጽሐፉን ታሪክ ተማሪዎቹ እንዲለምዱት ለማድረግ ማንበብ ነው። ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ የመማሪያ መጽሐፉን እራሣቸውን ችለው እንዲያነቡ ማድረግ ነው። ከሁለቱ አንደኛውን መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን ትኩረት ወደ አንድ ጥያቄ ወደ ሚመልስ ርእስ ማድረስ ነው። ከትምህርት ቤት ውጪ መጽሐፍ ቅዱስን የምትጠቀም ከሆነ

ይህ ተማሪዎችን ሊረዳ በሚችል መልኩ መቅረብ አለበት እንጂ የሚያሰለች ሥራ ወይም ፈተና መሆን የለበትም። ሥራው በሚሠራበት ወቅት አስደሣች፤ የሚያበረታታና ወደ አምልኮ የሚመራ መሆን አለበት። ይህ ጠቃሚና የሚያስደስት ሥራ ተግባራዊ ሲሆን ያበረታታል።

- **እዲታወስ -** በሚቻልበት ቦታ ሁሉ መልመጃዎች ወይም የመማሩን ሂደት የሚደግፉና ታሪክን እንደገና የምንከልስበት ሁኔታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ እንመክራለን።

- **አሳዩ -** በአንዳንድ ጥቂት አጋጣሚዎች የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎችን ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ታሪክን ለመረዳት በሥዕሎች ወይም በነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይጠቅማል። የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎች ታሪክን ለመናገር ጠቃሚዎች ናቸው። ለእያንዳንዱ ትምህርት ተገቢ የሆኑትን ምሥሎች ከሚከተለው ድህረ ገጽ www.freebibleimages.org ማውረድ ይቻላል። ሌላው የሚታይ መረጃ Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ሲሆን ይህንን ማስረጃ ግን ማግኘት የሚቻለው በግዢ ነው። ፎቶ ኮፒ በሚገኝበት ቦታ ጥቂት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ የሚያገለግሉ ሥዕሎችን ማድመቅ፤ ቀለም መቀባበትና ለትምህርት መጠቀም ይቻላል።

## ቁልፍ ጥቅሶችን ማስተማር

ጥቅሱ በልሙጥ ወረቀት ወይም በሠሌዳ ላይ የሚፃፍ ሲሆን ልጆቹ ጥቅሰቹ እስኪያዙና ቃላቶቹ እስኪያልቁ ሂደቱን መቀጠል ሲጠበቅባቸው ቃላቶቹ ካለቁም በኋላ ጥቅሰቹን ይደጋግማሉ።

መሪ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተለውን አካሄድ ተጠቀም።

1. ሁለት የፊደል ጨዋታ ተወዳዳሪ ቡድኖች ያስፈልጋሉ- የፊደላት ብዛት- የዋናው መሪ ጥቅስ ክፍት ቦታ ያለ ምንም ፊደላት ይቀመጥ- ልጆቹ የሚፈልጉትን ፊደላት እየመረጡ አንድ ልጅ ጥቅሱን እስኪያነበየው ድረስ ጨዋታው ይቀጥላል።
2. መጽሐፍ ቅዱስ በሚገኝበት ወቅት የመጽሐፍ ጥቅስ ጨዋታ ይካሄዳል። ልጆች ጥቅሱን ለማግኘት ይሽቀዳደማሉ፤ ጥቅሱንም መጀመሪያ ያገኘው ድምፁን ከፍ አድርጎ ያነባል።

## መርሀ ግብር

- ቅደም ተከተል:- በማስተማሪያ መመሪያዎች ውስጥ ያስቀመጥነው ቅደም ተከተል ለዚህ ትምህርት ቢያገለግልም አስተማሪው ቅደም ተከተሉን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀያይር ይችላል።
- መግቢያና ታሪክን ለመናገር - በግምት 15 ደቂቃዎች
- መሪ ጥቅሱን ለማስተማር - 5-10 ደቂቃዎች
- ወርክ ሺቱን ለማጠናቀቅ - 20 ደቂቃዎች
- ለሙከራና ሌሎች እንቅስቃሴዎች - 5-10 ደቂቃዎች ይበቃሉ።

ጠቃሚው አባባል ምን እንደሚል አስታውሱ:

"ብትነግረኝ ልረሣው እችላለሁ፤
ብታሣየኝ አስታውሰዋለሁ፤
ብታሣትፈኝ እረዳዋለሁ።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ሥርዓተ ትምህርት

| | ደረጃ 0 (ቅድመ-ት/ት)<br>ደረጃ 1 (እድሜ 5-7)<br>ደረጃ 2 (እድሜ 8-10) | ደረጃ 3 (እድሜ 11-13) | ደረጃ 4 (እድሜ 14+) |
|---|---|---|---|
| **የጀማሪዎች ስርዓተ ት/ት** | 1. የማሟሟቂያ ትምህርት- መግቢያ<br>2. ምዕራፍ 1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ምዕራፍ 2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ምዕራፍ 3 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የማሟሟቂያ ትምህርት- መግቢያ<br>2. ምዕራፍ 1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ምዕራፍ 2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ምዕራፍ 3 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የማሟሟቂያ ትምህርት- መግቢያ<br>2. ምዕራፍ 1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ምዕራፍ 2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ምዕራፍ 3 - የሉቃስ ወንጌል |
| **ስርዓተ ት/ት ሀ** | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የጥንት ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. ፀሎት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ፍጥረት እና ውድቀት<br>2. ጥንታዊ እድገት- ዘፍጥረት<br>3. ጴጥሮስ<br>4. የጴጥሮስ - መስቀል<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. ክርስቲያናዊ ኑሮ<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የገና ታሪክ |
| **ስርዓተ ት/ት ለ** | 1. የመጀመሪያው የክርስቶስ ኑሮ<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሣዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ ያገኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ምሣሌዎች<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የጥንት ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ፀሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የገና ታሪክ | 1. ምሣሌዎች<br>2. ተዓምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የጥንት ክርስቲያኖች<br>6. ያዕቆብ እና ቤተሠቡ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የሐዋሪያት ሥራ 2፤ 42 - የወደፊት መንገድ<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ህግ<br>12. የገና ታሪክ |
| **ስርዓተ ት/ት ሐ** | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሣሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ዮናታን<br>12. የገና ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ብዙ ተዓምራት<br>3. ብዙ ተዓምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሣሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሠው - ብሉይ ክዳን<br>12. የገና ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. የኢየሱስ ምሣሌዎች<br>3. የጌታ ሥልጣን<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሣሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. እያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሣ<br>11. ብዙ የብሉይ ኪዳን ባህርያት<br>12. የገና ታሪክ |

| | ለ1 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – ምሳሌዎች<br>ርእስ – ባልንጀራዬ ማነው? | ለ1 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – ምሳሌዎች<br>ርእስ – ሁለቱ ባለእዳዎች |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት*: ሉቃስ 10: 25-37***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 10: 27***<br>**የምንማረው:**<br>1. የእኛ ባልንጀሮች ፆታና ሀይማኖት ሳይወስናቸው የእኛን እርዳታ የሚሹ ናቸው።<br>2. እግዚአብሔርን መውደዳችንን ባልንጀሮቻችንን በመንፈሳዊ፣ በስጋዊ ወይም በሚያስፈልጋቸው ነገሮች በመርዳት ፍቅራችንን በተግባር መግለጽ እንችላለን። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: *ሉቃስ 7: 36-50***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሮሜ 5: 1***<br>**የምንማረው:**<br>1. በኢየሱስ ክርስቶስ እይታ እኛ ሁላችንም ባለ እዳ ነን ሁላችን ኃጢአትን ስለሰራን ለእግዚአብሔር ባለእዳዎች ነን።<br>2. ኃጢአታችን ይቅር ከተባለልን በመቀደስና በአገልግሎት ኢየሱስ ክርስቶስን ልንወደውና ጊዜ ልንሰጠው ይገባል። |
| **አስተዋውቁ** | የባልንጀራን ምንነትና ጥሩ ባልንጀራ የሚያደርገን ቅርበት ሳይሆን እርዳታችንን ለሚፈልጉ የምናሳየው ደግነትና ጓደኝነት እንደሆነ አስረዱ። | ቀጥሎ ያሉትን እንደሚያጠቃልል በመጥቀስ የምሳሌውን መነሻ አውጡ፡<br>• ሶስት የእውነት ያሉ ሰዎች-ኢየሱስ፣ኃጢአተኛዋ ሴትና ፈሪሳዊው ስምኦን<br>• ሶስት በምሳሌው ውስጥ ያሉ ሰዎች- አበዳሪው፣500 ብር ያበደረው ሰው፣50 ብር ያበደረው ሰው<br>• ሶስት ጥያቄዎች – ***ቁጥር 42፣ 44 እና 49*** |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br><br>**ማብራራት እና ማስረዳት፡**<br>*ይህ ምሳሌ እንዴት እንደሚተገበር አስረዱ፡*<br><br>1. ሀ) በሌቦች እጅ የወደቀው ሰው ***(ቁጥር 30)*** ለሞት እስኪቃረብ ድረስ ተደብድቧል፣ቆስሏል፤<br>ለ) አንድ ሳምራዊ ደግነት አሳየ ***(ቁጥር 33)*** ቁስሉን አሰረለትና እስኪመለስ ድረስ እንዲንከባከቡት አደራ ሰጠ። ***(ቁጥር 33-35)***<br><br>2. ሀ) በኤደን መንግስተ ሰማይ ውስጥ ሰው በመውደቁ ምክንያት እግዚአብሔር ሲያየን በኃጢአት የሞትን እንደሆንን ነው። ***(ኤፌሶን 2: 1)***<br>ለ) እግዚአብሔር ለእኛ እንደ ኃጢአተኝነታችን በሞቱ እንድንፈወስና ህይወታችን እንዲቀየር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ አለም በመላክ ደግነትን አሳየን። ኢየሱስ የመጣው ልክ እንደ ደጉ ሳምራዊ የእኛን ፍላጎት ለሟሟላት ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አንድን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ: ስዕል- የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br><br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. የስምኦን የራስ-ጽድቅ፣የሴቲቷ የንስሀ ለቅሶ፣ሀሴት፣ፍቅርና ምስጋና እናም ስምኦን ኢየሱስ "ይቺን ሴት ማራቅ ነበረበት" ብሎ ሲያስብ ሀሳቡን ማንበብ የሚችለው ጌታ ኢየሱስ። ***(ቁጥር 36-39)***<br>2. በዚህ ምሳሌ ለማሳየት የተፈለገው ኢየሱስ የእኛ አበዳሪ መሆኑን ነው። እኛ ሁላችንም ለእግዚአብሔር ባለእዳ ነን እናም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት እዳችንን ከፈለልን። ስምኦን ራሱን ያየው 50 ብር እዳ እንዳለበት ሰው ሴቷን ደግሞ 500 ብር እዳ እነዳለበት ሰው እንደሆነ ኢየሱስ አውቋል። ኢየሱስ የኃጢአት ትንሽና ትልቅ እንደሌለው ስምኦን እንዲያውቅ ፈልጓል። 50 ብር እዳ እና 500 ብር እዳ ያለባቸው ሁለቱም ሰዎች መክፈል ስላልቻሉ አበዳሪው ሁለቱንም ይቅር አላቸው አለው። ***(ቁጥሮች 40-43***)<br>3. ደጉን ብር አበዳሪ ከሁለቱ ባለ እዳዎች ማን አብልጦ እንደሚወደው ሲጠየቅ በብዙ ይቅር የተባለውን እንደሆነ መለሰ። (ቁጥር 42)ኢየሱስ የስምኦንን ትኩረት ወደዚች ሴት አደረገናለእርሱ ያላትን ፍቅር ስምኦን ለእርሱ ካለው ፍቅርና አለማክበር ጋር አወዳደረው። (ቁጥር 44) ኢየሱስ ይቅር ማለት እንደሚችልና ሴቷ የዳነችው በስራዋ ሳይሆን በእምነቷ እንደሆነ ተናገረ። ***(ቁጥሮች 48-50***)<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አንድን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ: የሚሆን ስዕል የለም** |
| **እዲታወስ** | ምሳሌው እንዴት እንደሚተገበር እንደተረዱት እርግጠኛ ለመሆን ሁሉንም ፈትኗቸው። | ***ሐዋ.ስራ 13፡ 38-39*** አንብቡና ኢየሱስ በዚህ ትምህርት ምን ሲያስተምር እንደነበር እንዴት እንደሚያጠቃልል አብራሩ።<br>***ኤፌሶን 4፡ 32*** አንብቡና ይቅር የተባሉ ሰዎች ለሌሎች እንዴት መሆን እንዳለባቸውና ለሁሉም ኃጢአታችን(እዳችን) በእግዚአብሔር ይቅር መባል እንዴትእንደሆነ ስሜቱ አብራሩ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ተማሪዎቹ ለውጥ ተሰምቷቸዋል?<br>2. ከተሰማቸው ቀጥሎ ለተጠቀሱት ሰዎች ጥሩ ባልንጀራ ወይንም ጓደኛ የሚሆኑባቸውን መንገዶች አስቡ፡<br>ሀ)ክርስቶስን ለማያምን ሰው (መንፈሳዊ)<br>ለ)አካል ጉዳተኛ ለሆነ ሰው(ስጋዊ)<br>ሐ)በአንዳንድ ቦታዎች የሚኖሩ በቂ ምግብ የሌላቸው ሰዎች(እቃ) | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ስምኦን ኢየሱስን ልዩነት በሌለው መንገድ ነው ያየውና ለኃጢአቱ ንስሀ መግባቱንና ይቅርታና ሰላም ማግኘቱን የሚያሳይ ነገር የለም። ***(ቁጥር 50)***<br>2. ስለ ኢየሱስ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው? ስለኃጢአታቸው ንስሀ ገብተው ይቅርታ ለማግኘት ወደ እርሱ መተዋል?<br>3. ይቅርታን ካገኙ ምርጥ የሆነውን ጊዜያቸውን፣ብቃታቸውንና ያላቸውን ነገር ለኢየሱስ ይሰጣሉ? ሴቷ እንዴት ምላሽ እንደሰጠች አብራሩ። |

| | ለ1 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – ምሳሌዎች<br>ርእሱ – ሀብታሙ ገበሬ | ለ1 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – ምሳሌዎች<br>ርእስ – ባልንጀራዬ ማነው? |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 12: 13-21***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 12: 15***<br>**የምንማረው፡**<br>1. ሀብታሙ ገበሬ የንብረት ሀብታም ሲሆን የመንፈስ ግን ደሀ ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔርን ከህይወቱ አስወጥቷል።<br>2. በህይወታችን ንብረትን ሳይሆን እግዚአብሔርን ስናስቀድም ትንሽም ሆነ ብዙ ቢኖረን እግዚአብሔር ህይወታችንን ለክብሩ ያደርገዋል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 10: 25-37 በተጨማሪም ፊልጵስዩስ 2: 1-11***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 10: 27***<br>**የምንማረው፡**<br>1. ፆታና ሀይማኖት ሳይገድበው የእኛን እርዳታ የሚሻ ሰው ባልንጀራችን ነው፥ ደግነት ማሳየት ደግሞ የእኛ ሀላፊነት ነው።<br>2. ልክ ደጉ ሳምራዊ እንዳደረገው ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ለይ ሞቱ እኛን ሊታደገን እና የማንሰጋበት ቦታ ለይ አስቀምጦ የሚያስፈልገንን ሊያሟላልን ይችላል።<br>በተጨማሪም ደረጃ 3 ትምህርት 1ን ተመልከቱ። |
| **አስተዋውቂ** | ስለሚወደዱ ንብረቶች አውሩ።<br>ስለ ምኞት ኃጢአት አውያዩና ስንሞት ይዘናቸው የማንሄዳቸውን ምድራዊ ነገሮችን በመስገብገብ  መሰብሰብ ራስወዳድነት መሆኑን እንደተረዱት አረጋግጡ።<br>አስሩን ህግጋት ተመልከቱና የመጨረሻውን አትመኙ የሚለውን አስረዱ።***(ዘፀአት 20: 17)*** | ባልንጀሮቻችን እነማን ናቸው ስለሚለው አውሩ።<br>ባልንጀራ መሆን የሚገናኘው ከቀረቤታ ጋር ሳይሆን ለሚፈልጉን ሰዎች ደግና ሰላማዊ ከመሆን ጋር እንደሆነ አብራሩ። እግዚአብሔር ሁሉም ልጆቹ  (በተለይ ክርስቲያኖች) የሚጠሏቸውንም ጨምሮለሁሉም ሰው ደግ እንዲሆኑ ይፈልጋል። |
| **አጠናቂ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ኢየሱስ ይህ ሰው መንፈሳዊ ነገር ከስጋዊና ከጊዜያዊ ነገር ይልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ስላልገባው ሞኝ ብሎ ይጠራዋል።<br>2. ሞኝ የነበረው በእነዚህ መንገዶች ነው፡<br>ሀ) እግዚአብሔር የሌለው - ህይወቱን ሚመራው ያለእግዚአብሔር ነበር። ህይወት ብዙ ነገር የሞላበት ቢሆን እንኳን እግዚአብሔር ከሌለበት ግን ባዶ ነው።ያለው ንብረት ሁሉ ከእግዚአብሔር የመጣ እንደሆነ አልገባውም ነበር።<br>ለ) ደሀ የሆነ ሞኝ- በእርግጥም ደሀ ሆኖ ሀብታም ነበር- ከዘላለም ህይወት አንፃር ደሀ ነው።ልቡን ከእግዚአብሔር ይልቅ በሀብት ለይ ነበር ያደረገው።<br>ሐ) ራስ ተኮር ሞኝ-  ***ከቁጥር 17-19*** ባለው ውስጥ 6 እኔ፣ 5 የእኔ እና 4 አደርጋለው የሚሉትን ቃላት አስተውሉ። ነፍሱን እንኳን ሳይቀር እንደራሱ አድርጎ “ነፍሴን!” ብሏል።<br>መ) ወደፊቱን የሚያይ ሞኝ- ስለ ወደፊቱ ሲያወራ በጣም ራስ ወዳድ ከመሆኑ የተነሳ ለሚቀጥሉት ብዙ አመታት ምንም እንደማይጎልበትና ዘና ብሎ እየበላና እየጠጣ የራሱን ስሜት እያረካ እንደሚኖር ነው። ***(ቁጥር 19)***<br>ሠ) የተፈረደበት ሞኝ- ረስቶት የነበረው እግዚአብሔር እንዲህ አለው “ነፍስህን ከአንተ ሊወስዷት ይፈልጓታል”። ***(ቁጥር 20)*** አዲስን ህይወት የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው የሚወስዳትም እራሱ ነው።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሁለትን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:  ስዕል- የሞኙ ሀብታም ምሳሌ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. የሙሴን ህጎች በደንብ አጥብቆ የሚያውቅ ሰው  የዘላለምን ህይወት ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለበት ኢየሱስን ጠየቀው። ኢየሱስም ወደ ህጉ አመልክቶ ምን እንደሚል ጠየቀው። የሚጠይቀው ለእግዚአብሔር እና ለባልንጀራ ሙሉ ፍቅር ነው። የአስርቱ ተእዛዛት ጥቅም እኛን ለማዳን ሳይሆን ምን አይነት ኃጢአተኞች እንደሆንን ሚያሳየን ነበር።<br>2. ጠበቃው ከእግዚአብሔር ደረጃ መውረዱን ተረድቶ ነው ኢየሱስ እንዲያድነው ጥያቄ ያቀረበው። “ባልንጀራዬ ማነው?” ብሎ በምላሹ ጥያቄ ጠየቀ ኢየሱስም ይህን ለመመለስ ብሎ የደጉ ሳምራዊውን ምሳሌ ተናገረ። የአይሁዱ ካህንና ሌዋዊው ሰው አይሁዶች ነበሩ፥አይሁድና ሳምራዊ ደሞ አይዋደዱም። እነሱ ሳይረዱት አለፉ። የተጠላው ሳምራዊ ግን የተደበደበውን ሰው ሊያነሳ ቀረበ። ጠበቃው ለተጎዳው ሰው እውነተኛ በልንጀራ የሆነው ሳምራዊው መሆኑን የግዱንም ቢሆን ተናገረ።<br>**3.** በካህኑና በሌዋዊው ህጉ ኃጢአተኞችን ለመርዳት ሀይል እንደሌለውና በደጉ ሳምራዊ ደግሞ እኛን ከኃጢአት ቅጣት ለማዳን ለእኛ ጥቅም ወደ እኛ የመጣውን ኢየሱስን ማየት እንችላለን።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሁለትን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:  ስዕል- የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ** |
| **እዲታወስ** | ሀብታሙ ገበሬ ሶስት ከባድ የሆኑ ጥፋቶችን ሰርቷል፡<br>1. የህይወትን አላማ ስቷል።***ፊልጲስዮስ 1: 21ን*** *አንብቡና የጳውሎስን የህይወት አላማ አስረዱ።*<br>2. ሀብቱን ለራሱ ነበር የተጠቀመው።***ፊልጲስዮስ 4: 19ን*** *አንብቡና የሌሎችን ፍላጎት ስናሟላ እግዚአብሔር እንዴት የእኛን ፍላጎት እንደሚሞላ አስረዱ።*<br>3. ለስጋው ባቻ ያስብ ነበርና ነፍሱን አጣ። ***ማርቆስ 8: 36-37ን*** *አንብቡና እንዴት ከሀብታሙ ነጋዴ ጋር እንደሚገናኝ አብራሩ።* | የፊልጵስዩስን ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ተመልከቱና ***1-4 ያሉት ቁጥሮች*** ለክርስቲያኖች የጥሩ ባልንጀራን ብቃቶች እንደሚያሳዩና ***5-11 ያሉት ቁጥሮች*** ደግሞ ኢየሱስ ለሁሉም በመሞቱ ተመሳሳይ የማይገኝለት የፍቅር ምሳሌ መሆኑን እንደሚያሳይ ትምህርቱን በማጠቃለል ግለፁ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ንብረቶቻችንን ሌሎችን ለመርዳት እንዴት እንደምንጠቀምባቸው በዝርዝር ፃፉ።<br>2. ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ለይ ያላቸውን እምነት ቅድሚያ መስጠትና ***(ዮሐንስ 3፡16)*** እርሱን በህይወታቸው አንደኛ ማድረግ አለባቸው። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>ሁሉም ሰው ባልንጀራችን ነው፡<br>1. ስጋዊ፣መንፈሳዊና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን በምን መንገድ ነው የምንረዳቸው?<br>2. ***ሉቃስ 6: 35*** ስለ ጥሩ ባልንጀራ ምንድን ነው የሚናገረው? እንዴት ነው ይሄ በተግባር የሚውለው? |

| | ለ1 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – ምሳሌዎች<br>ርእስ – ዘሪው | ለ1 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – ምሳሌዎች<br>ርእስ – ሞኙ ሰው |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ማርቆስ 4: 1-20***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ማርቆስ 4: 20***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው።<br>2. የተለያዩ አይነት መሬቶች የሰዎችን ልብ እንዴት የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚቀበሉ ይወክላሉ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 12: 13-21***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሉቃስ 12: 15***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. የአንድ ሰው ህይወት መመኘት ኃጢአት ነው።<br>2. ነፍስን እያጡ ሀብትን በመሰብሰብ ለይ ማተኮር የሚያስከትለው ውጤት አስፈሪ ነው።<br>በተጨማሪም ደረጃ 3 ትምህርት 2ን ተመልከቱ። |
| **አስተዋውቁ** | ኢየሱስ የሚያስተምራቸውን እውነቶች ለማግነን ሲል አብዛኛውን ጊዜ ምሳሌዎችን እንደሚናገር አስረዱ። ባጠቃላይ ምሳሌዎቹ ጥልቅ መንፈሳዊ ትርጓሜዎች አሏቸው። አንዳንዴ ምሳሌዎቹን አያስረዳም ነበር በዚህ ጊዜ ግን ሙሉ ማብራሪያ ነበር የሰጠው።<br>ዘሩ የተዘራባቸው የተለያዩ ቦታዎች ለእግዚአብሔር ቃል የሚሰጡ የተለያዩ ምላሶችን ይወክላሉ። | የዚህን ምሳሌ መሰረት አብራሩ። አንድ ሰው ኢየሱስን ባለመስማማት ውስጥ መሀል እንዲገባ እየጠየቀው ነው።ኢየሱስ ወደ አለም የመጣው ሰዎችን ለማዳን እንጂ ፈራጅ ለመሆን ለልጆች አስታውሱ። አንዳንድ ነገሮች ትኩረታችንን ከሚፈልግ ከመንፈሳዊ ነገር አንፃር ስናያቸው ምንም ዋጋ የላቸውም። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br>***ማብራራታ* እና *ማስረዳት*፡**<br>1. በመንገድ ዳር ያለው አፈር ***(ቁጥር 15)*** ጌታ ኢየሱስን እንቢ የሚሉ ሰዎችን ይወክላል። ሰይጣን ደሞ ቃሉን በሚወስዱት ወፎች ይመሰላል። እንደዚህ አይነት ሰው ለእግዚአብሔር ቃል ልዩነት የሌለው ሆኖ ይቀራል።<br>2. አለታማው መሬት ***(ቁጥር 16-17)*** እምነትን የሚያጠብቅና መከራ ከመምጣቱ በፊት በደህና የሚሄድን ሰው ይወክላል። መከራ ሲመጣና ለክርስቶስ መቆም ሲገባው ግን የሚያስከፍለው ዋጋ ትልቅ እንደሆነ ሲያይ ሁሉን ነገር ትቶ ይሄዳል። የመከራ ጊዜ ሲመጣ እምነቱ እውነት እንዳልሆነ ይረጋገጣል።<br>3. እሾሃማው መሬት ***(ቁጥር 18-19)*** ጥሩ ጅማሬ ያለውና እውነተኛ ክርስቲያን የሚመስልን ሰው ያሳያል።ነገር ግን የበለጠ የሚደሰተው በሀብትና በአለም ነገሮች ስለሆነ ምንም ፍሬ የለውም።<br>4. መልካሙ መሬት (***ቁጥር 20)*** ቃሉን የሚቀበል- ለኃጢአቱ ንስሀ የሚገባና እምነቱን በኢየሱስ ላይ ያደረገ-ምንም ዋጋ ቢያስከፍል እንኳን በታማኝነት የሚከተል ሰው ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሶስትን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:ስዕል- የዘሪው ምሳሌ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br>***ማብራራታ* እና *ማስረዳት*፡**<br>1. ይህ ምሳሌ የሚያሳየው ንብረት በህይወት ውስጥ ቁልፍ ነገር እንዳልሆነ ነው።ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው እናም ለእግዚአብሔር ክብር ልንጠቀመው ይገባል። ይህ ሰው ለተቸገሩት ያለውን መስጠት እንዳለበት ተረድቶ መሆን አለበት።<br>2. የወደፊት ህይወቱን አቅዷል። በእግዚአብሔር ለይ ምንም እንዳልተደገፈ ከተጠቀማቸው ቃላት ማየት እንችላለን "እኔ"፣"የእኔ" ***በቁጥር 17-19*** እግዚአብሔር ለዚህ ሰው ህይወት ሌላ እቅድ ነበረውና የዛን ቀን ማታ እንደሚሞት ነገረው።(***ቁጥር 20)*** ይህ ሰው ሞኝ ከመሆኑ የተነሳ ለዘለአለሙ አለም ምንም አልተዘጋጀም ነበር ያቀደው ነገር ሁሉም መና ሆኖ ቀረ-***በአሞጽ 4:12*** ያለውን ማስጠንቀቂያ ተመልከቱ።.<br>3. እግዚአብሔር በዚህ ምሳሌ ውስጥ ምን አይነት ከባድ ጥያቄ እንደጠየቀ አመልክቱ እንዲህ ይላል "ይህስ የሰበሰብከው ነገር ለማን ይሆናል?" ***(ቁጥር 20)*** ስጦታችንን እና ፀጋችንን ልንጠቀም የሚገባው የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስፋት እደሆነ ተናገሩ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሶስትን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:ስዕል- የሞኙ ሀብታም ምሳሌ** |
| **እዲታወስ** | ተማሪዎች በአራቱ አይነት መሬቶች መካከል ያለውን ልዩነት እንደተረዱት አረጋግጡ።የፍሬ ማፍራት ደረጃዎችን-ሰላሳ ስልሳና መቶ እጥፍ ***ቁጥር 20*** በማየት አብራሩና በጣም ፍሬያማ የሆነ ህይወት የሚኖሩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በፍቃደኝነት የሚያደርጉና እንደዚህም በማድረጋቸው የሚደሰቱ መሆናቸውን አስረዱ። | ***ምሳሌ 11: 4 እና 29*** እና ***ማቴዎስ 6: 19-21*** እንዴት ይህንን ትምህርት እንዳጠቃለሉ ተመልከቱ።በተጨማሪም ***ዘፀአት 20: 17*** ስለ ምኞት ይጠቅሳል። |
| **የተግባር *ሥራ*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. የትኛው መሬት ነው የእያንዳንዳችንን ልብ የሚወክለው?<br>2. ለክርስቲያኖች በት/ቤት ወይንም በሌላ ቦታ ለኢየሱስ የቆሙበት አጋጣሚ ምን ነበር?<br>3. እንደ ክርስቲያን ለጌታ ኢየሱስ ፍሬያማ ምንሆንባቸውን መንገዶች አስቡ።ወደ የትኛው ነው እኛ ልናድግ የሚገባው- 30፣ 60 ወይስ 100 እጥፍ? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. የህይወትን እውነተኛ አላማ "ለእኔ ህይወት ክርስቶስ ነው" (ጳውሎስ በ***ፊልጲስዮስ 1: 21)*** የማስጨበጥ አስፈላጊነት።<br>2. ያለንን ነገር ለሌሎች ጥቅም የማዋል አስፈላጊነት።<br>ሰዎችን ልትረዱበት የምትችሉበትን መንገዶች ዝርዝር ስሩ።<br>3. የመዳንን ጉዳይ ለሀብት በመስገብገብ አለመተካት ያለው አስፈላጊነት። |

| | **ለ1 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 4 – ምሳሌዎች**<br>**ርእስ – ሌሎችን ይቅር ማለት** | **ለ1 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 4 – ምሳሌዎች**<br>**ርእስ – የመጨረሻው ራት** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ማቴዎስ 18: 21-35***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ኤፌሶን 4: 32***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ይህ ምሳሌ የተነገረው ክርስቲያኖች እንዴት ይቅር ማለት እንዳለባቸው ለማሳየት ነው።<br>2. ሌሎችን ይቅር ለማለት ገደብ የለሽ መሆን አለብን። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 14: 15-24***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 6: 37***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. እግዚአብሔር "ወደ እኔ ኑ"(***ማቴዎስ 11: 28)*** ለሚለው ጥሪው ምላሽ ለሚሰጡ ሰዎች በሰማይ ድግስ አዘጋጅቷል።<br>2. ለመዳን ወደ ኢየሱስ የመጣን ሰዎች ሌሎች ሰዎችንም ለኢየሱስ ምላሽ እንዲሰጡ ማበረታታት አለብን። |
| **አስተዋውቁ** | ይቅር ስለማለት ጴጥሮስ የነበረበትን ችግር አስረዱ።እሱ የሚያውቀው በብሉይ ኪዳን ቢበዛ ሰው ሶስት ጊዜ ይቅር እንደሚባል መሆኑን አስረዱ። (***አሞጽ 2: 6***) የኢየሱስ ደቀመዝሙር በመሆኑ ከሌላው ይልቅ ደግ ሊሆን እንደሚገባው ስላሰበ ሰባት ጊዜ ብሎ ሀሳብ አቀረበ። ***(ቁጥር 21***) ነገር ግን ኢየሱስ "ሰባ ጊዜ ሰባት" አለ።ይህ ማለት ያለ ገደብ ይቅር ልንል ይገባል ማለት ነው። | በምስራቅ ያሉ ሰዎች የታቀደ ድግስ ካዘጋጁ ጥሪ የሚያደርጉት ሁለቴ ነበር። የመጀመሪያው ጥሪ የሚያመለክተው ዝግጅት እንደሚያስፈልግ ነው። ሁለተኛው ደሞ ድግሱ ዝግጁ መሆኑን ለማሳየት ነበር። በዚህ ጊዜ ሰዎቹ መገኘት ስላልፈለጉ ላለመገኘት ምክንያት አቀረቡ። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. የሰራተኞቹ ጌታ የተበደረው ሰራተኛ እዳውን መክፈል እንደከበደው ተረድቶ በደግነት እዳውን ሁሉ ተወለት። ***(ቁጥር 25-27)*** ሰራተኛው የሚገባውን ቅጣት በመተዉ ያሳየው ምህረት ነው።<br>2. እንደ ኃጢአተኛ ያለብንን የኃጢአት እዳ ልንከፍል ስለማንችል ከእግዚአብሔር ቅጣት ለማምለጥ የእግዚአብሔር ምህረት ያስፈልገናል።መዳንን ልናገኝ የምንችለው ክርስቶስ የአለምን የኃጢአት እዳ ለመክፈል በመስቀል ላይ በሰራው ስራ ነው።እግዚአብሔር ልጁን ሰጠ።እሱም ነፍሱን ስለ ብዙዎች ቤዛ አደረገ። ***(ማቴዎስ 20: 28)***<br>3. ይቅር የተባለው ሰራተኛ በስሩ ያለው ተበዳሪ እሱ ከነበረበት አንፃር (1ሚሊዮን ብር) በጣም ትንሽ እዳ ስለነበረበት (5 ብር) ይቅር ሊለው ይገባ ነበር። ለእርሱ ግን የተደረገለትን ምህረት ረሳ።<br>4. ጌታ ኢየሱስ ለእኛ እንደሚሆነው ሁሉ እኛም ለሌሎች መሆን አለብን።የእርሱ እንደሆንን የምናስብ ከሆነ ለሌሎችና ለጠላቶቻችንም ጭምር ይቅርታ ልናደርግ ይገባል። ***(ቁልፍ ጥቅሱን ተመልከቱ)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አራትን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:ስዕል- ይቅር የማይለው ሰራተኛ ምሳሌ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ታላቁ ራት የሚያስታውሰን ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት የመዳንን ስራ እንደጨረሰና በውጤቱም የወንጌል ግብዣ ወደ ሁሉም እንደ ተሰራጨ ነው።<br>2. ሶስቱ ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም።ለሶስቱም ለመገኘት ቢፈለግ ኖሮ ማመቻቸት ይችሉ ነበር።<br>የመጀርያው ምክንያት ***(ቁጥር 18)*** ይቅርታ እየጠየቀ ነው። አንድ አይሁድ ግን ሳያይ መሬት ይገዛል ለማለት ይከብዳል።የራቱ ጊዜ ማታ ስለሆነም ሊያየው እንደማይችል ይናገራል።ሁለተኛው ምክንያት ***(ቁጥር 19)*** ይሄኛው ሰው ትንሽ እንቢተኛ በመሆኑ ምንም ይቅርታ አላቀረበምና ለበሬዎቹ ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ተሰማው።ሶስተኛው ምክንያት***(ቁጥር 20***)ይሄ ሰው የማይመጥን ምክንያት ነው የሰጠው ነገር ግን በጣም ራስ ወዳድ ባይሆን ኖሮ ሚስቱን ወደ ድግሱ ይዞ መምጣት ይችል ነበር።<br>3. የመጀመሪያው ምሳሌ የሚወክለው ልባቸውን ንብረት ላይ የሚጥሉ ሰዎችን ነው።ሁለተኛው ምሳሌ በስራ በጣም ጊዜያቸው ለተያዘ ሰዎችና ሶስተኛው ምሳሌ ደግሞ የቤት ውስጥ ሀላፊነታቸው ጊዜያቸውን የወሰደባቸው ሰዎችን ነው።<br>4. ጋባዡ ተናደደ በምክንያታቸውም እንደተሰደበ ተሰማው።ሰራተኞቹንም ጠርቶ በመንገድ ዳር ሄደው ደሀዎችን፣ተራና እውር የሆኑ ሰዎችን እንዲጠሩ አዘዛቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አራትን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:ስዕል- የታላቁ ራት ምሳሌ** |
| **እዲታወስ** | ይሄ ክፍል እንዴት ምህረትንና ፀጋን እንደሚያሳይ አስረዱ። ***ቲቶ 3: 5*** አጥኑ "እንደ ምህረቱ መጠን አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ስራ አይደለም" እና ምህረት ከእግዚአብሔር ቁጣ ምናመልጥበትን የጽድቅ መንገድ እንደሚከፍት አስረዱ።***ኤፌሶን 2: 8*** አጥኑ "ፀጋው በእምነት አድኖአችኋልና" መዳን በፀጋ በኩል የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ እኛ ልንገዛው የማንችለውንና የማይገባንን ዘላለማዊ ጥበቃ ሰጠን። | ምሳሌው መጀመርያ ተግባር ለይ የዋለው አይሁዶች ወንጌልን ሲገፉ የተሻለ ምላሽ ለሰጡት አህዛብ ጥሪ እንዴት እንደተደረገ አብራሩ። ይህም ለተማሪዎች ያለውን ጠቀሜታ እንደተረዱ አረጋግጡ። የእግዚአብሔርን ምህረትና ፀጋ መግፋታቸውን የሚቀጥሉ ሰዎች አንድ ቀን ይረፍድና የወንጌሉ ድግስ በሮቹም በሰማይ እንደሚዘጉ ተናገሩ።<br>በዚህ ዘመን ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሲገፉ የሚያቀርቧቸውን ምክንያቶች አስቡ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ይህ ትምህርት ይቅር ስለማለት እንዴት ነው ሚፈትናችሁ?<br>2. እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር ከተባልን ሌሎችን ይቅር ማለት ለምን አስፈለገን?<br>3. ይቅር ከማለት በተጨማሪ ሌላ ምን ብቃት ሊኖረን እንደሚገባ ከ***ኤፌሶን 4: 32*** ተመልከቱ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ማንም የግብዣ ጠረጴዛው ላይ ለመቀመጥ ብቁ ያልሆነ ሰው እንደሌለ ከመንገድ ዳር ከተጠሩት ሰዎች ማየት እንችላለን።<br>2. ሁሉንም ወደ መዳን ባርኮት ለማምጣት በፍቅር መሳብ ይኖርብናል።አሁንም ወደ እግዚአብሔርን መንግስት እንዲገቡ ለሰዎች በቂ ቦታ አለ። |

| | **ለ2 - ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 1 – ተአምራቶች**<br>**ርእስ – ውኃን ወደ ወይን** | **ለ2 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 1 – ተአምራቶች**<br>**ርእስ – ውኃን ወደ ወይን** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዮሐንስ 2: 1-11***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 2: 11***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ልንታዘዘው የሚገባው ጌታ ኢየሱስን ነው።<br>2. ጌታ ኢየሱስን ስናምነው ሀሴትን ወደ ህይወታችን ይመጣል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዮሐንስ 2: 1-11***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 15: 14፣ ዮሐንስ 2: 5***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስን የምንወደው ከሆነ ማርያም በሰርጉ ቦታ ሰራተኞቹን "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" ***(ዮሐንስ 2: 5)*** ብላ ያዘዘቻቸውን ልንሰማ ይገባል።<br>2. ይህን ተአምራት ሲያደርግ ኢየሱስ በዚያ ለነበሩት ሁሉ በሰው ሰውነት ውስጥ ሆኖ ግን እግዚአብሔር እንደሆነ እየገለጠና ደቀመዝሙሩ ያላቸውን እምነት እያጠነከረ ነበር። |
| **አስተዋውቁ** | በሩቅ ምስራቅ አካባቢ ስለሚደረጉ ሰርጎች አውሩ።<br>በዚህ ክፍል ***በቁጥር 1 ላይ*** ማርያም "የኢየሱስ እናት" ተብላ እንደተጠራች አስረዱ። ኢየሱስ ታዋቂ የሆነው የድንግሏ ማርያም ልጅ ስለሆነ አይደለም ነገር ግን ማርያም ታዋቂ የሆነችው የጌታ ኢየሱስ እናት ስለሆነች ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሁሌም ትልቁን ቦታ ለጌታ ኢየሱስ እንጂ ለማርያም እንደማይሰጥ አሳውቁ። | ተአምራቶች ምን እንደሆኑና ለምን ወንጌላት መጽሐፍት ለይ እንደተጠቀሱ አስረዱ።<br>የዮሐንስ ወንጌል ሰባት በህዝብ ፊት የተደረጉ ተአምራቶችን ይዙአል።አንደኛውም በቃና ገሊላ ሰርግ ለይ የተደረገው ነው።ሌሎቹም የንጉስ ቤቱ ሹም ልጅ መፈወስ፣በቤተሳይዳ ገንዳ አጠገብ የተፈወሰው ሽባ ሰው፣5000 ህዝብ መመገብ፣ኢየሱስ በባህር ለይ ሲራመድ፣የአይነስውሩ መፈወስ፣የአልዓዛር ከሞት መነሳትን ያጠቃልላል።ከትንሳኤው በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ብቻ የተደረገ 153 አሳዎችን የማጥመድ ስምንተኛ ተአምራት ነበር። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ኢየሱስን ወደ ሰርጉ መጋበዛቸው በጣም ጥሩ ውሳኔ ነበር።እኛም ወደ ልባችን፣ወደ ቤታችን፣ወደ ማህበራዊ ህይወታችንና ወደ ትምህርት ቤት ህይወታችን እርሱን መጋበዝ የተመረጠ ውሳኔ ነው።<br>2. ገና ሰርጉ ከመጀመሩ ወይኑ በማለቁ እንግዶቹ ተናደው ነበር።ነገር ግን በዚያ ሁኔታ ለእርዳታ ወደ ኢየሱስ ተመለከቱ።<br>3. ምርጥ የሆነው ወይን እስከመጨረሻው ቆየ።ይህ የክርስትና ህይወት ሁሌም የተሻለ እየሆነ እንደሚመጣ ያሳየናል።<br>4. ይህ ተአምራት ከርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አሳየ።በተጨማሪም የደቀመዛሙርቱን እምነት አጠነከረ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አንድን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ: ስዕል- ኢየሱስ በሰርግ ቦታ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስ፣እናቱና ደቀመዝሙሩ ውኃው ወደ ወይን በተለወጠበት የሰርግ ቦታ ሁሉም እንግዶች ነበሩ።<br>2. ማርያም ሰራተኞቹን ከሌላ ሰው ይልቅ በተሻለ መልኩ ሊታዘዙት ወደሚገባው ወደ ኢየሱስ አመጣቻቸውና በመጨረሻ በተፃፈው ቃሏ "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ!" አለቻቸው።<br>3. በዚህ ሰርግ መጨረሻ ምርጥ የሆነው ወይን ቀረበ ነገር ግን የተለመደው ምርጥ የሆነውን ወይን መጀመርያ ማቅረብ ነበር።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አንድን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:ስዕል- ኢየሱስ በሰርግ ቦታ** |
| **እዲታወስ** | ልጆቹ በደረጃ 3፣ ለ2 ትምህርት 1 ለይ ያሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲረዳቸው ይህን ተአምራት በፈተና መልክ ከልሱ። | ከላይ የተጠቀሱትን እያንዳንዱን ነጥቦች ከክርስቲያናዊ ህይወት ተግባር ጋር በማያያዝ ትምህርቱን ከልሱ። አስቡ፡-<br>1. ወይን በመጽሐፍ ቅዱስ ሀሴትን ነው ሚገልፀው።ማርያም "ምንም ወይን የላቸውም" ***(ቁጥር 3)*** ስትል እያወራች የነበረው በጌታ ኢየሱስ ጭራሽ አምነው ስለማያውቁ ሰዎች ነው። የማያምኑ ምንም ዘላቂ ደስታ የላቸውምና።<br>2. ጌታ ኢየሱስን የሚወዱ በቃሉ-መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን ነገር ያደርጋሉ። |
| ***የተግባር ሥራ*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ጌታ ኢየሱስን ወደ ልባችን መጋበዝ ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ። ***ምሳሌ 3: 5-6ን*** አንብቡና ጌታ ለእርሱ ጠቃሚ የሆነን ህይወት እንድንኖር እንዴት እንደሚረዳን ተመልከቱ።<br>2. ***ምሳሌ 16: 11ን*** አንብቡና ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉ ሰዎች በመንግስተ ሰማይ ምን እንደሚጠብቃቸው ተመልከቱ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛችን እንዴት ማመን እንዳለብን ሀሳብ ውሰጥ አስገቡ።<br>2. ለህይወታችን የእግዚአብሔርን እቅድ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና በየጊዜው መፀለይ ያላቸውን ጥቅም አስረዱ። |

| | ለ2 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – ተአምራቶች<br>ርእስ –የልጁ መፈወስ | ለ2 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – ተአምራቶች<br>ርእስ – የልጁ መፈወስ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዮሐንስ 4: 43-54***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዮሐንስ 4: 50***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. የንጉስ ቤቱ ሹም ልጅ በጣም ታሞ ለሞት ተቃርቦና ከኢየሱስም በርቀት ላይ ነበር ነገር ግን ኢየሱስ ፈወሰው።<br>2. ሁላችንም ስንወለድ ኃጢአተኞችና ከኢየሱስ በርቀት ያለን ነን ነገር ግን ንስሀ ስንገባና ይቅርታ ለማግኘት ወደ እርሱ ስንዞር አዲስን ህይወት ሊሰጠን ይችላል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዮሐንስ 4: 43-54***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሐዋ.ስራ 16: 31; ሮሜ 10: 9***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. የንጉስ ቤቱ ሹም ልጅ ወደ ስጋዊ ሞት ተቃርቦ ነበር ወደ ህይወት ሊመልሰው የሚችለው ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው።<br>2. በመንፈሳዊ ሀሳብ የእኛ ኃጢአት ለመንፈሳዊ ሞት የሚዳርግ በሽታ ነው፤ ኢየሱስ ብቻ ነው ዘላለማዊ ህይወትን ሊሰጠን የሚችለው። |
| **አስተዋውቁ** | ጌታ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቃና ሲሄድ ውኃን ወደ ወይን ቀይሮ እንደ ነበር ተማሪዎችን አስታውሱ አሁን ደሞ ሌላ የበለጠ ተአምራትን በቃና አደረገ-የንጉስ ቤቱ ሹም ልጅ ፈወሰ።<br><br>ኢየሱስ በቃና እንደነበረ ነገር ግን ልጁ በቅፍረናሆም እንደነበር ለማሳየት ትምህርቱ ላይ ያለውን ካርታ ተጠቀሙ።በአካል በዚያ ባይገኝም እንኳን የኢየሱስ ሀይል ባለበት በታ ሆኖ ተሰምቶት ነበር። | ጌታ ኢየሱስ የመጀመሪያውን ተአምራት ያከናወነው በቃና እንደነበረና ዝናውም እንደገነነ ተማሪዎችን አስታውሱ።በጣም ከመታወቁ የተነሳ በሄሮድስ ቤተ-መንግስት ሹም የነበረው የልጁ አባት ልጁን እንዲፈውስለት በትህትና ጠየቀው።<br>የንጉስ ቤቱ ሹም ልጁ እንዲፈወስ ጌታ ኢየሱስ በአካል ልጁ አጠገብ መሆን እንዳለበት ነበር ያሰበው።<br>ጌታ ኢየሱስ ለዚህ እምነት ማጣቱን አይቶ አልገሰፀውም ነገር ግን ላሳየው እምነት ምላሹን ሰጠው ደግሞም የበለጠ አደረገለት።ኢየሱስ በተአምራቶች ላይ የተመሰረተ እምነት ሳይሆን በቃሉ ላይ ብቻ የተመሰረተ እምነት ደስ እንደሚያሰኘው ተናገሩ በመጀመሪያ እመኑ ከዚያም እዩ!። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br><br>1. የዚህ ልጅ አባት አይሁድና የንጉስ ሄሮድስ ተቀጣሪ ነበር።ከሌሎቹ አይሁዶች የበለጠ በኢየሱስ ላይ እምነት የነበረው ይመስላል እናም ልጁ በጣም ታሞ ስለነበር እንዲፈውስለት ወደ ጌታ ኢየሱስ በመሄድ ለመነው።<br>2. የልጁ አባት ልጁ እንዲፈወስ ጌታ ኢየሱስ በአካል አጠገቡ መሆን እንዳለበት ነበር ያሰበው ነገር ግን ኢየሱስ ልጁ እንደተፈወሰ ነገረው።አባትየውም የኢየሱስን ቃል አምኖ ወደ ቤት መጓዝ ጀመረ።ልጁ ስንት ሰአት ላይ እንደተፈወሰ ሰራተኞቹን ሲጠይቅ መልሳቸው ልክ ኢየሱስ ልጅህ ተፈውሷል ባለው ሰአት መሆኑን አረጋገጡለት።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: የሚሆን ስዕል የለም** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br><br>1. **የታመመው ልጅና የአባትየው ጥያቄ።** በሽታና ሞት ደሀ ሆንን ሀብታም ወደ ሁላችንም መምጣቱ አይቀርም ነገር ግን መንፈሳዊ ፍላጎትን ለሟሟላት ለሁሉም ኢየሱስ ያስፈልጋል።ኢየሱስ ኃጢአትን በበሽታ ይመስለዋል ***ማቴዎስ 9: 12-13ን*** ተመልከቱ።ጌታ ኢየሱስን የሚያውቁ የዘላለም ህይወት እንዳላቸውና የማያውቁት ደግሞ የዘላለም ህይወት እንደሌላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ***(1 ዮሐንስ 5: 10-14***)<br>2. **የጌታ ምላሽ።** ጌታ ኢየሱስ “ልጅህ በህይወት አለ” ***(ቁጥር 50)***ብሎ ሲነግረው የሹሙን እምነቱን እየፈተነ ነበር።የዚያን ጊዜ የነበሩት ሰዎች ልክ አሁን ላይ እንዳሉት ሰዎች በእምነት የእግዚአብሔርን ቃል ከመቀበል ይልቅ ምልክትና ተአምራትን ***(ቁጥር 48)*** ይፈልጉ ነበር፤ መጀመርያ እምነት ከዚያ ማየት።<br>3. **ውጤቱ።** የእግዚአብሔር ቃል ህያው ነውና በእርሱ የጌታ ኢየሱስን ማንነት ወደማወቅ መምጣት ብቻ ሳይሆን በእርሱ እንበረታለን ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ቃል ጀርባ ያለው ሙሉ የእግዚአብሔር ሀይል ነው። ሹሙ ልጁ መፈወሱን አመነ በውጤቱም ሙሉ ቤተሰቦቹ አመኑ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: የሚሆን ስዕል የለም** |
| **እዲታወስ** | ቁልፍ ጥቅሱን እወቁ ***ዮሐንስ 4: 50*** እና የኢየሱስ ሀይል የሹሙን ልጅ መፈወሱ ብቻ ሳይሆን የሹሙ ሙሉ ቤተሰብ በኢየሱስ እንዳመኑ***(ዮሐንስ 4: 53)*** አወያዩና ጥቅሱ እንዴት ትምህርቱን እንደሚያጠቃልል አሳዩ። | ***ዕብራውያን 11: 6ን*** “ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም” ተመልከቱና አሁን ተማሪዎች ከተማሩት ጋር በምን እንደሚገናኝ አብራሩ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ለዘለአለም ህይወት ሁላችንም ጌታ ኢየሱስን ልናምነውና ልንታዘዘው ይገባል።<br>2. እንደ አዳኒ ክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ ተአምራትን ለማድረግ ወይንም ፀሎትን ለመመለስ በአካል መገኘት እንደማይጠበቅበትና እርሱ በየትኛውም በታና ጊዜ አላማውን መፈፀም መቻሉን ልናደንቅ ይገባል። በፀሎት ህይወታችን ይህ ሊያበረታታን ይገባል። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ሹሙ ጌታ ኢየሱስን አምኖ ወደ ቤቱ ለመሄድ ጉዞ ጀመረ። እምነቱን በተግባር እያሳየ ነበር።በቤትና በት/ቤት ውስጥ እምነታችንን በተግባር የምናሳይባቸውን መንገዶች አስቡ።.<br>2. እምነታችንን በኢየሱስ ላይ ማድረግ አሁን የምንኖርበት ባህል ላይ እንዴት ነው ተፅእኖ የሚያሳድረው ? (መጀመርያ እምነት ከዚያም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለህይወታችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማየት ከሚለው ጋር ተቃራኒ የሆነ ለማመን መጀመርያ ማየት አለብን የሚል የሰዎች አስተሳሰብ ተመልከቱ።) |

| | ለ2 ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – ተአምራቶች<br>ርእስ – የታወሩ አይኖች በሩ | ለ2 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – ተአምራቶች<br>ርእስ – አይነ ስውሩ በርጠሜዎስ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ማርቆስ 10: 46-52***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማርቆስ 10: 52***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. በርጠሜዎስ በጣም ጠቃሚ ነገር ይፈልጋል።የሚያስፈልገውን ነገርም ያውቃልና ጌታ ኢየሱስ ይህ ጉድለቱ እንዲያሟላለት ይፈልጋል።<br>2. ጌታ ኢየሱስ የበርጠሜዎስን ፀሎት መለሰ እናም በርጠሜዎስ ጌታ ኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም ባደረገው የመጨረሻ ጉዞው ለይ በመከተል ምስጋናውን አሳየ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ማርቆስ 10: 46-52***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማርቆስ 10: 52***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ልክ በርጠሜዎስ እንደ ተጠራው ሁላ ***(ቁጥር 49)*** ጌታ ኢየሱስ ወንጌልን በመስበክ መንፈሳዊ እውሮችንም ይጠራል።<br>2. ለመዳን በጌታ ኢየሱስ ስናምን የኃጢአት ህይወታችንን ወደ ኋላ ትተን ልንከተለው ይገባል። |
| **አስተዋውቁ** | አይነ ስውር የሆነ ሰው የሚያውቁ ከሆነ እንደዚህ አይነት ሰዎች በህይወታቸው ምን አይነት ከባባድ አጋጣሚዎች ሊገጥማቸው እንደሚችል ተማሪዎችን ጠይቁ።ዓይነ ስውር ሰዎች ሊረዱ ይችላሉ ነገር ግን እውርነት ሊድን እንደማይችል አብራሩ። | ጌታ ኢየሱስ በነበረበት ጊዜ ለአይነ ስውሮች በጣም ትንሽ እንክብካቤ ነው ሊኖር የሚችለውና አብዛኞቹ ለመኖር ሲባል ለልመና ተዳርገው እንደነበር አብራሩ።አሁን ካለው ሁኔታ ጋር አስተያዩ። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br>***ማብራራታ* እና *ማስረዳት*፡**<br>1. አይነስውር የነበረ በርጠሜዎስ የሚባል አንድ አይሁድ ኢየሱስ መሲህና የዳዊት ልጅ እንደሆነ ያምን ነበር።አይሁዶች ግን ባጠቃላይ ይህን አያምኑም ነበር።<br>2. በርጠሜዎስ ማየት ይችል ዘንድ ለእርዳታ መጮሁን ቀጠለ እናም የሰማይና የምድር ፈጣሪ አለማትን ያፀናው ኢየሱስ የለማኙን ጩኸት ሰምቶ በመቆም(ቁጥር 49) እይታውን መለሰለት።<br>**3.** ከመሰቀሉ በፊት ወደ እየሩሳሌም ባደረገው የመጨረሻ ጉዞ ለይ የኢየሱስ ታማኝ ተከታይ በመሆን በርጠሜዎስ ምስጋናውን አሳየ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል - ኢየሱስ አይነ ስውሩን በርጠሜዎስ ፈወሰ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br>***ማብራራታ* እና *ማስረዳት*፡**<br>1. በርጠሜዎስ እውርም ደሀም ነበረ ይህም እኛ ለመንፈሳዊ ነገሮች እውሮች እንደሆንን ያስታውሰናል።በዚህም ምክንያት ወዴት እንደምንሄድ አናውቅም።<br>2. ይህ በርጠሜዎስ ኢየሱስን ሊያገኝበት የሚችለው የመጨረሻ እድሉ ሊሆንም ይችላል እናም በቅንነት ኢየሱስን "ማረኝ" ***(ቁጥር 47)*** ብሎ የጠየቀው።ከተጠቀሰው "እኔ" ከሚለው ተውላጠ ስም መዳን የግል ነገር መሆኑን እንረዳለን።<br>3. በርጠሜዎስ ወደ ጌታ ኢየሱስ ከመሄድ የሚያግደውን ነገር ሁሉ ጣለና ስለ አይኑ ሲጠይቅ በፍጥነት ጥያቄው ተመለሰለት። "የመጀመርያ እይታ" ጌታ ኢየሱስን በአንዴ ተከተለው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል - ኢየሱስ አይነ ስውሩን በርጠሜዎስ ፈወሰ** |
| **እዲታወስ** | ወደ በርጠሜዎስ አጭር ፀሎት ***በቁጥር 51*** እና ወደ ኢየሱስ ፈጣን ምላሽ ***በቁጥር 52*** ሀሳባቸውን ሳቡ።ልክ ኢየሱስ ፍላጎቱ ምን እንደነበር በርጠሜዎስን እንደጠየቀው በጌታ በኢየሱስ በአስቸኳይ ለምን ማመን እና እርሱን መከተል እንዳለብን እንማራለን ምክንያቱም ይህን እድል የማናገኝበት ጊዜ ይመጣል።በርጠሜዎስ ይህ እድል አምልጦት ቢሆን ኖሮ ጌታ ኢየሱስን በድጋሜ መቼም ላያገኘው ይችል ይሆናል። | ***ማቴዎስ 4: 18-22ን*** ተመልከቱና የሚሰሩትን ሁሉ በፍጥነት ትተው ኢየሱስን የተከተሉትን ሌሎች ሰዎች ለዩ።<br>ኢየሱስ ከሚከተሉት ሰዎች ምን ምን ብቃቶችን እንደሚጠብቅ ***በኤፌሶን 6: 10-18*** እና ***በቆላሲያስ 3: 8-17*** ተመልከቱ።<br>ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ክርስቲያናዊ ህይወትን የሚገልፁ ስድስት ዋና ዋና ባህርያትን በዝርዝር ፃፉ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. አንድ አይነ ስውር አይሁድ እውነተኛ መንፈሳዊ አይን እንዳለውና እርሱን ለመከተል ዝግጁ መሆኑን ሲያይ ኢየሱስን አስደስቶት ይሆናል።ሁሉም ሰው በኢየሱስ አምኖ እርሱን በመከተል ምስጋናን ማምጣት ይኖርበታል።<br>2. ፀሎቶቻችን ረዥም መሆን አይጠበቅባቸውም።ጌታ ኢየሱስን እንደምንወደው ልንነግረውና ምን እንድናደርግለት እንደሚፈልግ ልንጠይቀው እንችላለን።<br>3. ሁሉም አንዳንድ አጭር፣ስለራሳቸው የግል ፍላጎት የሆነ አስፈላጊ ፀሎት እንዲያዘጋጁ ጠይቁ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. እየጠራን እያለና ሰአት ባለን ጊዜ ለመዳን ጌታ ኢየሱስን የመፈለግን ጥቅም።<br>2. የጌታ ኢየሱስ ተከታዮች ስንሆን የእርሱ ሀይል በህይወታችን ይሰራል እና ፍቃዱን በማድረግ እርሱን ማስደሰት እንችላለን።ከድሮው ኃጥአተኛ ህይወታችን ጋር ጨርሰናል እናም ከጌታ ኢየሱስ ጋር አዲስን ህይወት ጀምረናል።<br>3. ***ዮሐንስ 8: 12ን*** አንብቡና የድሮውን ጨለማ ትቶ "በብርሀን ውስጥ መሄድ" ምን ማለት እንደሆነ አስቡ። |

| | ለ2 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – ተአምራቶች<br>ርእስ - የአስሩ ለምፃሞች መፈወስ | ለ2 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – ተአምራቶች<br>ርእስ – አስሩ ለምፃሞች |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ሉቃስ 17: 11-19***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***መዝሙር 107: 8***<br><br>**የምንማረው:**<br>1. ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው ከኃጢአታችን ሊያነፃን የሚችለው።<br>2. የነፁ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን በፍቅርና በመሰጠት በማገልገል ምስጋናቸውን ሊያሳዩ ይገባል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ሉቃስ 17: 11-19***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ኤፌሶን 2: 8-9***<br><br>**የምንማረው:**<br>1. ሁላችንም ስንወለድ ኃጢአተኞች ነንና የኃጢአት በሽታ ሊፈወስ የሚችለው በጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው።<br>2. በጌታ ኢየሱስ በማመን ከኃጢአት በሽታ ስንፈወስ ስለ በረከቱ፤ማዳኑና በየቀኑ ከእርሱ ስለምንቀበለው መልካም ነገሮች ሁሉ እርሱን ሁልጊዜ ልናመሰግነው ይገባል። |
| አስተዋውቁ | ለምጽ የቆዳ በሽታ እንደሆነና አሁንም በአለም ዚሪያ ብዙ ሰዎችን እንደሚያጠቃ አብራሩ።<br><br>***ዘሌዋውያን 13: 45-46ን*** ተመልከቱና በሙሴ ዘመን ለምፃሞች እንደ ቆሸሹ እንደሚቆጠሩና ብቻቸውንም መኖር እንደነበረባቸው አብራሩ። | ለምጽ በአለማችን ላይ እስከ ዛሬም ያለ በጣም የሚሰራጭ የቆዳ በሽታ መሆኑን አብራሩ።20 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች በዚህ በሽታ እንደተጠቁ ይገመታል። ስለ 'The Leprosy Mission' ሰምተው ሊሆን ይችላል - በእንደዚህ አይነት በሽታ የተጠቁ ሰዎችን ለመርዳት የተቋቋመ ድርጅት ነው።<br><br>ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በለምጽ የተሰቃዩ ሌሎች ሰዎችን ተመልከቱ።በተጨማሪም ***ዘሌዋውያን 13: 45-46ን*** ተመልከቱ። |
| አጠናቁ | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት:**<br>1. ለምፃሞቹ ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዲቀላቀሉ አይፈቀድላቸውም ነበር ስለዚህም በርቀት ሆነው ምህረትን ለማግኘት ወደ ጌታ ኢየሱስ ጮሁ።<br>2. ጌታ ኢየሱስን በመታዘዝ ለምፃሞቹ ወደ ካህኑ ቤት ለመሄድ ተነሱ።ቤቱ ጋርም ሲደርሱ ከለምፃቸው ተፈውሰው ነበር።<br>3. ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ የፈቀዱላቸው ካህናቶቹ ነበሩ።<br>**4.** ሳምራዊ የሆነው አንድ ለምፃም ብቻ ጌታ ኢየሱስ ስለፈወሰው ለማመስገን ተመለሰ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል-ኢየሱስ አስሩን ለምፃሞች ፈወሰ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት:**<br>1. ለምፃሞቹ ራሳቸውን ሊያድኑ አልቻሉም ነበር ነገር ግን ወደ ትክክለኛው ሰው ወደ ጌታ ኢየሱስ ለምህረት መጡ። ***(ቁጥር 13)***<br>2. ጌታ ሂዱ ***(ቁጥር 14)*** ሲል ለምፃሞቹ ቃሉን በመስማታቸው ወደ ካህኑ ቤት በመሄድ ላይ ሳሉ ከለምፃቸው ነፁ።መታዘዝና ጌታ በተናገረው ቃል ላይ ያለ እምነት መንፃትን አመጣ።<br>3. ሳምራዊ የሆነው አንድ ለምፃም ብቻ ጌታ ኢየሱስ ስለሰጠው የመንፃት ስጦታ ለማመስገንና ለማምለክ በትህትና ተመለሰ። ***(ቁጥር 16)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል- ኢየሱስ አስሩን ለምፃሞች ፈወሰ** |
| እዲታወስ | • ለምጽ የሚያሳየን ከጌታ ኢየሱስ በርቀት ያለ ኃጢአተኛ ማንነትን እንደሆነ በመናገር ትምህርቱን አጠናቁ።ከኃጢአታቸው ሊነፁ የሚችሉት ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባል ጌታ ኢየሱስን ሲጠሩና ለወንጌል ታዛዥ ሲሆኑ ብቻ እንደሆነ ለሁሉም አስታውሱ።<br>• ትምህርቱ የሚያሳየን አንዴ ከኃጢአት ከነፃን ሁልጊዜ ስለ መዳናችን ጌታ ኢየሱስን ልናመሰግን እንደሚገባ ነው።ምስጋና ጌታ ኢየሱስን የሚወዱ ሰዎች ምልክት ነው። | ትምህርቱን ለመከለስና ተማሪዎችን የጥናቱን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ለማዘጋጀት ያክል ፈተና ፈትኗቸው። |
| የተግባር ሥራ | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ***የ1 ዮሐንስ 1: 7ን*** ጥቅም ሀሳብ ውስጥ አስገቡ።<br>2. ስለሞተላቸው ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስን ሊያመሰግኑ ይገባል።<br>3. የቡድን ስራ – ልናመሰግንባቸው የሚገቡ ምክንያቶችን ዝርዝር ስሩና ለእያንዳንዱ የሚሆን ፀሎት ፃፉ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ተማሪዎቹ ልክ እንደ ዘጠኙ ወይንስ እንደ አንዱ ናቸው የሚለውን አስቡ።<br>2. ምስጋና ማቅረብ በትክክል ምን ማለት እንደሆነና ህይወታችን ላይ እንዴት ተጽእኖ ማምጣት እንዳለበት አብራሩ። ***መዝሙር 40: 3***<br>3. የቡድን ስራ – ልናመሰግንባቸው የሚገቡ ምክንያቶችን ዝርዝር ስሩና ለእያንዳንዱ የሚሆን ፀሎቶችንም ፃፉ። |

| | **ለ3 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 1 – ቢታኒያ**<br>**ርእስ – ሁለት እህትማማቾች** | **ለ3 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 1 – ቢታኒያ**<br>**ርእስ – በቤት ውስጥ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 10: 38-42***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 10: 42***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስ ከአገልግሎታችን ይልቅ ለእርሱ ያለንን ፍቅር ዋጋ ይሰጠዋል።<br>2. የቤት ወይንም የት/ቤት የህይወት ግዴታዎቻችን በፀሎት ህይወትና የእግዚአብሔርን ቃል በምናነብበት ሰአት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር አይገባም። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 10: 38-42***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማርቆስ 6: 31***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. እንደ ክርስቲያን ለማደግና እግዚአብሔር ምን እያለን እንደሆነ ለመስማት ከተጨናነቀ ቀናችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ጊዜ መውሰድ ይኖርብናል።<br>2. በተጨማሪም እግዚአብሔርን ለማዋራትና ስለመልካምነቱ ሁሉ ለማመስገን እናም በህይወታችን ምሪትን ለመጠየቅ ከቀናችን ውስጥ ጊዜ መውሰድ ያስፈጋል። |
| አስተዋውቁ | ተማሪዎች የምንወደው ሰው ቤት ሲመጣ ምን ያህል ደስ እንደሚል እንዲያስቡት ጠይቁ።የማርያምና የማርታ ቤት ኢየሱስ ከጎበኛቸው ቤቶች ውስጥ አንዱ ነበር። ኢየሱስ የጎበኛቸውን ሌሎች ጥቂት ቤቶች ለማወቅ መነሳሳት አለበት፡ ***ሉቃስ 4: 38፣ ሉቃስ 7: 37፣ ሉቃስ 8: 51፣ ሉቃስ 19: 5***. የእኛ ቤት ጌታ የሚከበርበትና የሚመሰገንበት ስፍራ ሊሆን ይገባል። | ማርያምም ማርታም ኢየሱስን ይወዱት እንደነበረ አብራሩ።በዚህ አጋጣሚ ሁለቱም እርሱን በማገልገል ላይ ነበሩ።ማርታ በጣም ስራ በማብዛቷ እንግዶቿን እየገፋች እንደሆነ አላስተዋለችም ነበር፤ጌታ ኢየሱስ እርሱን ለመስማትና ከእርሱ ለመማር ጊዜ አልነበራትም። በህይወታቸው ቅድሚያ የሚሰጡት ነገር ምን እንደሆነ ተማሪዎችን ጠይቁ።ስራ ማብዛት ፀሎትንና መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን መተኪያ እንዳልሆነ ተማሪዎችን አስረዱና መረዳታቸውንም አረጋግጡ። |
| አጠናቁ | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ማርታ ሰራተኛና ማርያም ደግሞ አገልጋይ ሆነው ሳለ ስራና አገልግሎት ግን አንድ ላይ የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። *የማምለክን ትርጉም አብራሩ።*<br>2. ማርታ ብዙ አይነት ምግብ በማቅረብ ጌታ ኢየሱስን ለማስደሰት ብታስብም እንኳን እርሱ "የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው" አለ፥ አንድ አይነት ምግብ በቂ ነው ማለት ነው።በጣም የሚፈልገው ህብረታቸውን ስለነበር ነው ማርያምን "እሷ የተሻለውን መርጣለች" ***(ቁጥር 42)*** ብሎ የተናገረው። ለመንፈሳዊ ህይወታችን የሚያስፈልገው ምግብ ለስጋችን ከሚያስፈልገው ምግብ ይልቅ በጣም ጠቃሚ ነው እናም ጌታ ኢየሱስ ማርታና ማርያም ቃሉን መስማት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ እንዲረዱ ፈልጓል። ***(1 ጴጥሮስ 2: 2)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አንድን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:የሚሆን ስዕል የለም** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ጌታ ትኩረቱን ያደረገው ፀሎትና ቃሉን ማጥናት ላይ ነው።ሁለቱ ነገሮች ለህይወታችን በረከት በጣም መሰረታዊ ነገሮች ናቸው።<br>2. ማርታ ለቤትስራ ስለተጨነቀች ኢየሱስ አልወቀሳትም ነገር ግን ለሚገባው ነገር ቅድሚያ ባለመስጠቷ በስርአት ተናግሮ አስተካከላት።<br>3. ጌታ ኢየሱስ ***በቁጥር 42*** ላይ አስፈላጊው ነገር እርሱ ላይ ማተኮር እንደሆነ አሳይቷል።ከአገልግሎታችን ይልቅ ለእርሱ ያለንን ፍቅር ያስበልጣል።ጌታ ማርታዎች ከመሆን ማርያሞች ወደ መሆን እንድንሄድ ይፈልጋል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አንድን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:የሚሆን ስዕል የለም** |
| እዲታወስ | ማርያም በኢየሱስ እግር ስር እንደተቀመጠች መመልከት ደስ ይላል። ***(ቁጥር 39)*** ማርያም ዝቅ ብላ በትህትና ያን ስፍራ በመውሰዷ ለጌታ ኢየሱስ እንዴት የሚገባውን ክብርና ሙገሳ እንደሰጠች አብራሩ።<br>1. እኛም ጌታ ኢየሱስን በህይወታችን ልናከብርበትና ልናሞግስበት ምንችልባቸውን መንገዶች ጠይቁ።<br>2. ቀጥሎ በተዘረዘሩት ክፍሎች ውስጥ ያሉት ሰዎች በሙሉ በኢየሱስ እግር ስር ተገኝተው የሚያውቁ ናቸው- ***ማቴዎስ 28: 9፣ማርቆስ 5: 22፣ ሉቃስ 7: 38፤ ሉቃስ 8: 35።*** እነዚህን ጥቅሶች በመመልከት ሰዎቹ ማን እንደነበሩ በማየት ሁሉም በኢየሱስ እግር ስር የመገኘታቸውን ጥቅም አብራሩ። | ይህን ጥናት ለመከለስ ቀጥሎ ያሉትን በማሳየት ቁልፍ ጥቅሱን ተጠቀሙ፡<br>1. ጌታ ኢየሱስን የምንሰማበት ትክክለኛ ጊዜ አለ። ***(ማርቆስ 6: 31)***<br>2. ለጌታ ኢየሱስ የምንሰራበት ትክክለኛ ጊዜ አለ። ***(ማርቆስ 6: 7-13) (ሮሜ 12: 1)***<br>3. በፀሎት በታገዘ ህይወት የሚየገለግሉትን እንደሚባርክ ጌታ ቃል ገብቷል። ***(ኢሳያስ 40: 31)*** |
| የተግባር ሥራ | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. በእያንዳንዱ ቀን ህይወታችን እንዴት ነው የአምልኮ እና የስራ ጊዜያችንን ምናመጣጥነው?<br>2. ለጌታ ክብርና ምስጋናን በሚሰጥ አይነት ህይወት ለመኖር?<br>3. ብዙ ከማገልገል ይልቅ በደንብ ስለመገልገል ማሰብ?<br>4. ስራ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከማንበቢያና ከፀሎት ጊዜ እንደማይቀድም ለማረጋገጥ? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ፀሎትና መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን በእያንዳንዱ ቀን ቅድሚያ በመስጠት ጊዜያችንን ማመጣጠናችንን ለማረጋገጥ?<br>2. ለጌታ ኢየሱስ ያለን አገልግሎት ፍሬ የሌለው ስራ ማብዛት እንዳይሆን ለእርሱ መሰጠታችን ላይ ክፍተት እንደማያመጣ ለማረጋገጥ? |

| | ለ3 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – ቢታንያ<br>ርእስ – ሀዘን ወደ ደስታ ተለወጠ! | ለ3 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – ቢታንያ<br>ርእስ – መቃብሩ ጋር |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ዮሐንስ 11: 1-7 እና 17-44***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ዮሐንስ 11: 25***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው የሞተውን ወደ ህይወት ለማምጣት ሀይል ያለው።<br>2. ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው ለኃጢአተኞች (በሐዋርያው ጳውሎስ ***በኤፌሶን 2: 1*** ለይ "በበደልና በኃጢአት ሙታን" ተብለው ለተገለፁት) የዘላለምን ህይወት መስጠት የሚችለው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ዮሐንስ 11: 1-44***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ዮሐንስ 11: 25-26***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. በጌታ ኢየሱስ ሀይል አማካኝነት የአልዓዛር ከሙታን መነሳት በሞት ለይ ያለውን ሀይል ለማሳየት አስፈላጊ ነበር እናም ትንሳኤ ለክርስትና እምነት ወሳኝ ነገር ነው። ኢየሱስ ራሱን ብቻ ሳይሆን ***(ዮሐንስ 10: 18)*** ሌሎችን ከሞት የማስነሳት ሀይል አለው።<br>2. ኢየሱስ ፊትለፊት በማልቀስ ***(ቁጥር 35)*** በመከራችንና በሀዘናችን ከእኛ ጋር እስከማልቀስ ድረስ እንደሚያስብልን አሳየ። |
| **አስተዋውቁ** | ኢየሱስ ያደረጋቸውን አንዳንድ ተአምራቶች ተማሪዎች እንዲያስታውሱ ጠይቁና የትኞቹ ተአምራቶች በጣም አስደናቂ ሊባሉ እንደሚችሉ አብራሩ።<br>ይህ በኢየሱስ የአደባባይ ለይ አገልግሎት የመጨረሻው ተአምራት ነበር።አንዳንዶቹ አይሁዶች ጌታ ኢየሱስ እውር የነበረውን ሰው ማብራት ስለቻለ ለምን አልዓዛር እንዲሞት እንደፈቀደ ጠየቁት። ***(ቁጥር 37)*** እንደዛ ማድረግ ይችል ነበር ነገር ግን ***በቁጥር 25፡*** "ትንሳኤ እኔ ነኝ።" ያለውን የቃሉን እውነትና ሀይል እያሳየ ነበር። | የአልዓዛር ከሞት መነሳት በዮሐንስ ወንጌል ለይ ካሉት ሰባት ተአምራቶች የመጨረሻውና በዚያ ለነበሩ ለብዙ አይሁዶችም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲቀበሉና በእርሱ እንዲያምኑ ምክንያት እንደሆናቸው በማስረዳት ጥናቱን አስተዋውቁ። ነገር ግን አንዳንድ አይሁዶች ተአምራቱን ቢያዩም እንኳን አላመኑም እናም በቢታንያ ስለተፈጠረው ነገር ለፈሪሳዊያን ሄደው ተናገሩ።ጌታ ኢየሱስን ለመግደል እያሰቡ ነበር።በዚህ ዘመንም እንደዚህ አይነት ነገር እንዳለ ለተማሪዎች ተናገሩ-ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደሆነና ተአምራትን ማድረግ እንደሚችል የሚያምኑ በተቃራኒው ደግሞ ይህን የማይቀበሉና ተአምራት ማድረጉንም የሚክዱ አሉ። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. በቢታንያ የነበረው የማርያም፣የማርታና የአልዓዛር ቤት ኢየሱስ መገኘት ከሚወድበት ቤቶች ውስጥ አንዱ ነው።ጌታ ኢየሱስ በቤታቸው (በልባቸው) በህይወታቸው ውስጥ መኖሩን ተማሪዎችን መጠየቅ ይቻላል።***ራእይ 3: 20***<br>2. ልክ ጌታ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት እንዳስነሳው መንፈሳቸው ሙት ለሆነም ሰዎች አዲስና ዘላለም የሚኖር መንፈሳዊ ህይወትን ሊሰጣቸው ይችላል።<br>3. ይህ ታሪክ የሚያሳየን ጌታ ኢየሱስ የሚያዝንልን አዳኝ እንደሆነ ነው "ኢየሱስ እንባውን አፈሰሰ" ***(ቁጥር 35)*** እናም በዚያን ቀን የነበሩ አይሁዶች ኢየሱስ አልዓዛርን ምን ያህል እንደሚወደው ማየት ቻሉ። ***(ቁጥር36)*** እነሱንም ይወዳቸዋል ነገር ግን አብዛኛዎቹ ይህን አልተረዱም ነበር።<br>4. ኢየሱስ ከመቃብር ውስጥ አልዓዛርን ሲጠራው አዲስ ህይወት ነበረው፣ከተገነዘበት ጨርቅ ተላቆ ነበር ***(ቁጥር 44)*** እናም በህይወቱ ለጌታ ኢየሱስ ሀይል ህያው ምስክር ሆነ።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሳ (I)** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ማርያምና ማርታ የኢየሱስን ተአምራቶቹን ስላዩ ወንድማቸው በሞተ ጊዜ ለእርዳታ ወደ እርሱ ዞሩ።<br>2. ኢየሱስ ይህን ቤተሰብ ይወድ ነበር ነገር ግን ለጥሪያቸው ቶሎ ምላሽ አልሰጠም።አልዓዛር የሞተው የኢየሱስን በሞት ለይ ያለውን ሀይል ለደቀመዛሙርቱና በዚያ ለተገኙት አይሁዶች ለማሳየት ነበር ።<br>3. ኢየሱስ ያለቀሰው የአልዓዛር አለመኖር ስለተሰማው ነበር።<br>4. ኢየሱስ ያወራው ለሞተ ሰው ነበረ፤ እሱ ግን ሰማና መለሰ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሁለትን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሳ (I)** |
| **እዲታወስ** | 1. ልክ አልዓዛር አዲስ ህይወት እንደተሰጠው ሁሉ ***(ከቁጥር 44-45)*** በጌታ ኢየሱስ የሚያምኑም አዲስ ህይወት ይሰጣቸዋል።ጌታ ኢየሱስ "ለሙታን" ኃጢአተኞች እንዴት "አዲስ ህይወት" እንደሚሰጥ ለማወቅ ***ቆላሲያስ 2: 13 እና 2 ጢሞቴዎስ 1: 10ን*** ተመልከቱ።<br>2. የአልዓዛር አዲስ ህይወት የጌታ ኢየሱስ ሀይል በህይወቱ ለይ የሰራውን ስራ ማሳያ እንደሆነ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑትም ለእርሱ የሚኖሩበትን ሀይል ይሰጣቸዋል። ***(ኤፌሶን 2: 10)*** | በህይወታችን ካሉ ሙከራዎች ጋር በማያያዝ ጥናቱን ከልሱ እና ጌታ ኢየሱስ እንዴት ከመጥፎ አጋጣሚ ጥሩ ነገርን እንደሚያወጣ አሳዩ። ***ሮሜ 8: 28ን*** ተመልከቱ።የጌታ መዘግየት ግድ የሌለውና ምላሽ የማይሰጥ እንደሆነ ሊያሳስበን ይችላል ነገር ግን ታጋሽ መሆንን መማር ይኖርብናል። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. "በአዲስ ህይወት ውስጥ ለመራመድ" ንስሀ ስለመግባትና ወደ ጌታ ኢየሱስ ስለ መመለስ? ***(ሮሜ 6: 4)***<br>2. ወንጌልን ለሌሎች በማካፈል፣በት/ቤት ውስጥ ንቁ ተማሪ በመሆን፣ለወላጆች ታዛዥ በመሆንና ምናልባትም በመጠመቅ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ስለመሆን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. አማኞች ሞት ሊገዛውና ሊያጠፋው የማይችለው መንፈሳዊ ህይወት ነው ያላቸው።ይህ ማረጋገጫ ህይወታችንን ለጌታ ኢየሱስ አስገዝተን እንድንኖር ሊያደርገን ይገባል። ***ፊሊጲስዮስ 1: 21-23***<br>2. ይህ ተአምራት ጌታ ኢየሱስ በሀዘናችን ከእኛ ጋር እስከማልቀስ ድረስ ግድ እንደሚለው ያሳየናል። |

| | ለ3 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – ቢታንያ<br>ርእስ – ሌላ ጉብኝት | ለ3– ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – ቢታንያ<br>ርእስ – ጠረጴዛው ጋር |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ዮሐንስ 12: 1-11***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡ *1 ዮሐንስ 4: 19***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስን የእውነት ስንወደው ለእርሱ ምስጋናችንን ምንገልጽበትን መንገዶች እንፈልጋለን።<br>2. ለጌታ ኢየሱስ ማድረግ በምንችለው ነገር ላይ መቼም ቢሆን መዘግየት የለብንም ምክንያቱም ምን ያህል አጭር ወይም ምን ያህል ረዥም ጊዜ ልናገለግለው እንደምንችል አናውቅም። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ዮሐንስ 11: 55-57፣ 12 :1-11***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡ *መዝሙር 95: 6***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ለጌታ ኢየሱስ ብንሰጠው የሚበዛበት ምንም ነገር የለም። የእኛ በጣም ምርጥ የሆነው ነገር የሚገባው ነው!<br>2. ጌታ ኢየሱስን የምንወደው ከሆነ በአዲስ ኪዳን ላይ የሰጠንን ትእዛዞች በመፈፀም እንጓዛለን። |
| አስተዋውቁ | ቢታንያ ጌታ ኢየሱስ እንዴት ልዩ የሆኑ ጊዜያትን ያሳለፈበት ቦታ እንደሆነ አብራሩ።<br>በማርያምና በማርታ ቤት ጌታ ኢየሱስ የአምልኮን አስፈላጊነት እንዳስተማረ ተማሪዎችን አስታውሱ።<br>በትምህርት 2 ላይ አልዓዛርን ከሞት ባስነሳበት ጊዜ ኢየሱስ እርሱ "ትንሳኤ" መሆኑን አሳይቷል።<br>በዚህ ትምህርት ጌታ ኢየሱስ በቢታንያ በሚገኝ አንድ ቤት ውስጥ ማእድ ላይ ነበር። | ***በዮሐንስ 12: 1-11*** ያለው ይህ አጋጣሚ ***በማርቆስ 14: 3-9*** ካለው ጋር ተመሳሳይ ተደርጎ ነው የሚታሰበው።ማርያም ራስ ወዳድ ሳትሆን በጣም ውድ የሆነ ሽቶ እግሩን በመቀባት ባደረገችው አምልኮ ጌታ ኢየሱስ አሞገሳት።<br>ሽቶዎችና ቅመሞች በቀብር ሂደት ላይ ትልቅ ሚና አላቸው- ***ዘፍጥረት 50: 2-3ን*** አንብቡ።<br>***በቁጥር 7*** ላይ ማርያም ላሳየችው መሰጠት ኢየሱስ ለቀብሩ ዝግጅት እንደሆነ በማመልከት ምላሽ ሰጠ። |
| አጠናቁ | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር መሆኑ፣አብሯቸው ማእድ መቁረሱና ጓደኝነቱን ማጣጣማቸው ለማርያም፣ለማርታና ለአልዓዛር መታደል ነበር። ***(ቁጥር 2)***<br>2. ማርያም የጌታ ኢየሱስን እግር ውድ በሆነ ዘይት ቀብታ በፀጉሯ በማበሷ የተሰጣት ልዩ ቦታ ***(ቁጥር 3)*** የሚያሳየን ለእርሱ ብንሰጠው የሚበዛበት ምንም ነገር እንደሌለና የእኛ ምርጥ የሆነው ነገር ሁሉ እንደሚገባው ነው።<br>3. ይሁዳ ዘይቱ ተሽጦ ብሩ ለድሆች ቢሰጥስ ብሎ ሲያስብ ***(ቁጥር 5)*** ጌታ ኢየሱስ ሰዎች ደግነት ሊያደርጉላቸው የሚችሉበት በምድር ላይ ሁሌም ቢሆን ደሀ ሰዎች እንደሚኖሩ አሳሰበው።ለኃጢአተኞች ለመሞት ወደ መስቀሉ እየተቃረበ ስለሆነ ይህን ዘይት በጌታ ኢየሱስ ላይ የማፍሰስ እድሉ በጣም ጠባብ ነው።<br>4. መሪ የነበሩት ካህናት አልዓዛርን ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር። ***(ቁጥር 10)*** አልዓዛርን ሊገድሉት የፈለጉት ትንሳኤውን ስለካዱ እና የጌታ ኢየሱስ የትንሳኤ ምስክር ስለሆነ ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል – ማርያም ኢየሱስን ቀባችው** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. **ቤቱ** - በቢታንያ ውስጥ የሚገኘው ቤት (***ቁጥር 1)***<br>(ሀ) የአገልግሎትና የትእዛዝ (ለ) የአምልኮና የህብረት እና (ሐ)የሞትና የትንሳኤ ቦታ መሆኑን አሳዩ።<br>2. **ድግሱ *(ቁጥር 2)*** "ለእርሱ" ነበር።ማርያም፣ማርታና አልአዛር እርሱን እንደ ክቡር እንግዳ ቤታቸው ውስጥ ለመገናኘት ሁሉም አይነት ምክንያት አላቸው።<br>3. **በቅባቱ *(ቁጥር 3)*** ማርያም ጌታ ኢየሱስን እንደምትወደው አሳየች፤ ፍቅረ ዋጋ በመክፈል ይገለፃልና።<br>4. **አስተያየቱ *(ቁጥር 7-9)*** ከተሰጠው ሁሉ የሚበልጥ ነበር እናም ኢየሱስ ይህ አምልኮ በታሪክ ሁሉ እንደሚነገር አመለከተ- ***ማቴዎስ 26: 13ን*** አንብቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል – ማርያም ኢየሱስን ቀባችው** |
| እዲታወስ | ይህ ታሪክ ***በማርቆስ 14: 3-9*** ላይም ተደግሟል-ጌታ እግሩን ስለቀባችው ሴት ምን እንዳወራ ለማወቅ ***ቁጥር 8ን*** አንብቡ። ማቴዎስ ይህን ታሪክ እንዴት እንደፃፈው ***ማቴዎስ 26: 6-13*** ላይ አንብቡ እና ጌታ ኢየሱስ እንዴት ወደፊት ወንጌል እንደሚሰበክ መተንበይ ብቻ ሳይሆን የዚችም ሴት ስራ አብሮ እንደሚታወስ መናገሩን ተመልከቱ። | በጥናት ሶስት ለተጠየቀው ጥያቄ በቂ የሆነ መልስ ለመስጠት እንዲረዳቸው ይህንን ጥናት ስትከልሱ ተማሪዎችን ጥያቄዎች ጠይቋቸው። |
| የተግባር ሥራ | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. እናንተ ለጌታ ለኢየሱስ ያላችሁ ፍቅር እንዴት ነው ሌሎች ላይ ተጽእኖ ሚያሳድረው?<br>2. ብዙዎቹ አይሁዶች በጌታ ኢየሱስ አምነዋል ***(ቁጥር 11)*** ምክንያቱም በአልዓዛር አዲስ ህይወት ውስጥ ሀይሉን ማየት ይችሉ ነበር።ጌታ ኢየሱስን የምትወዱት ከሆነ ሌሎች በእርሱ እንዲያምኑ በህይወታችሁ ተጽእኖ ማሳደር የምትችሉት እንዴት ነው? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. **ቤቱ** – ከላይ በቁጥር አንድ በተጠቀሱት ነገሮች በኩል ጌታ ኢየሱስ በቤታችን አለ?<br>2. **ድግሱ** –ለአንድ አማኝ ጌታ ኢየሱስ በህይወቱ ከሁሉ የላቀ ነው?<br>3. **ቅባቱ** – ጌታ ኢየሱስን ምን ያህል ነው የምንወደው? ምርጥ የሆነውን ነው የምንሰጠው?<br>4. **አስተያየቱ** – ጌታ ማርያም ማድረግ የምትችለውን እንዳደረገች ተናገረ። (***ማርቆስ 14: 8)*** |

| | **ለ3 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 4 – ቢታንያ**<br>**ርእስ – ወደ እየሩሳሌም** | **ለ3 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 4 – ቢታንያ**<br>**ርእስ – ወደ እየሩሳሌም መንገድ ለይ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 19: 28-44***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 1: 12***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም ሲገባ ተከታዮቹ በመሀከላቸው ስላደረጋቸው ታላቅ ስራዎች በሙሉ እርሱን በማወደስ መዘመር ጀመሩ።<br>2. ኢየሱስ ለእየሩሳሌም አለቀሰ ምክንያቱም ሰዎቹ አልተቀበሉትም ለእርሱም ምንም ቦታ አልነበራቸውም። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 19: 28-41***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 1: 12***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. የእርሱ ከሆንን ጌታ ኢየሱስ እምነታችንን፣ ፍቅራችንን፣ አምልኮአችንን፣ አገልግሎታችንን እና ንብረታችንን ለራሱ ክብርና ምስጋና ያደርገዋል።<br>2. ጌታ ኢየሱስን ወደ ልባችንና ህይወታችን መጋበዝ በጣም አስፈላጊ ነው አንድ ቀን ይህንን እድል ለማግኘት በጣም ይረፍዳልና። |
| **አስተዋውቁ** | የሆሳእና ቀን ዝምብሎ በእድል የመጣ እንዳልሆነ አስተዋውቁ።ከአመታት በፊት ትንቢት ተነግሮለታል። ***ዘካሪያስ 9: 9ን*** ተመልከቱ፤ የጌታ ኢየሱስ የድል አገባብ ከመፈፀሙ ከ500 አመታት በፊት ተነግሮ ነበር። | ሰላም የሚሆንላቸውን ጌታ ኢየሱስን እንደ መሲህ የመቀበል እድላቸውን ስላሳለፉ ለእየሩሳሌም እንዳለቀሰ (***ቁጥር 41-42***) በማመልከት ጥናቱን አስተዋውቁ ።አሁን በጣም ረፍዶ ነበር እናም ጌታ ኢየሱስ በሚመጡት አመታት በአይሁድ ህዝብ ለይ ስለሚሆነው ከባድ ነገር አስጠነቀቀ።<br>ጌታ ኢየሱስ እንደ ተናገረው በ30 ዓ.ም (***ሉቃስ 19: 43-44)*** የሮማኑ ጄነራል እየሩሳሌምን ከበባት (70 ዓ.ም) ቤተመቅደሱን አፈራረሰ ነዋሪዎቹንም ጨፈጨፈ።ጌታ ኢየሱስ እየሩሳሌምን የጎበኘው መዳንን ለመስጠት ነበር ነገር ግን ለእርሱ ምንም ቦታ አልነበራቸውም ስለዚህም አስፈሪ ነገር ሊመጣ ነበር። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. የጌታ ኢየሱስ የድል አገባብ ***(ከቁጥር 28-40)።***<br>2. ደቀመዝሙሩ በምስጋና አፋቸውን ከፈቱ።***(ቁጥር 37)*** “በሰማይ ሰላም” እንጂ “በምድር ሰላም” ብለው እንዳልጮሁ አስተውሉ ምክንያቱም የጌታ ኢየሱስ ሞት እና ማረጉ “በሰማይ ሰላምን” ያመጣልና።ምንም “በምድር ሰላም” አይኖርም ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስን የሰላም አለቃ ሊገድሉት ነበርና።<br>3. ኢየሱስ ለእየሩሳሌም አለቀሰ ምክንያቱም ሰዎቹ አልተቀበሉትም ደግሞ በጣም ረፍዶ ድላቸውም አምልጧቸዋል። ***(ቁጥር 42)***<br>4. ኢየሱስ በ70 ዓ.ም እየሩሳሌምና በውስጧ ያሉት ሰዎች “የጉብኝታቸውን ዘመን ባለማወቃቸው” ***(ቁጥር 44***) ማለትም ጌታ መዳንን አቅርቦላቸው ነበር እነርሱ ግን ባለመፈለጋቸው ምክንያት በሮማኑ ጀነራል በቲቶ ስር ሆነው እንደሚጠፉ ተናገረ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዪ: ስዕል – በታላቅነት መግባት**<br>**ኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም ገባ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. **ወደ እየሩሳሌም መግባት- በዘካርያስ 9: 9** ለይ እንደተነገረው ጌታ ኢየሱስ ከሰው በተዋሱት ውርጫ ለይ ሆኖ ወደ እየሩሳሌም ገባ።ኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም ያደረገውን የድል አገባብ የተመለከቱ ሰዎች በእርግጥም ከ500 አመት በፊት የተነገረው ትንቢት በኢየሱስ መፈፀሙን አይተዋል።<br>2. **ወደ እየሩሳሌም የገባበት ጊዜ-**ኢየሱስ እስራኤል በሙሉ ወደ እየሩሳሌም ለፋሲካ በአል የሚሰበሰቡበትን ጊዜ ነበር የመረጠው።<br>3. **የሰዎቹ ተስፋ-** ሰዎቹ የህዝብ መሪ ይሆናል ብለው የጠበቁትን ንጉስ ስለሰጣቸው እግዚአብሔርን እያመለኩና እያመሰገኑ ነበር።ነገር ግን እርሱ ዘላለማዊውን መንግስት እየሰራ እንደሆነ ሲያዩ በእርሱ ለይ ተነሱበት።<br>4. **የፈሪሳውያኖቹ ምላሽ-** ፈሪሳውያኖቹ በአደባባይ ለይ ስለ ተመሰገነ ኢየሱስን ወቀሱት እና ሰዎቹን ፀጥ እንዲያሰኝም ጠየቁት።ኢየሱስም ከድንጋይ በላይ ደንዳና በመሆናቸው ወቀሳቸው!<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዪ: ስዕል – በታላቅነት መግባት**<br>**ኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም ገባ** |
| **እዲታወስ** | ታሪኩን ተመልከቱና አሁን ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ የማመን አስፈላጊነትን አብራሩ። **2 ቆሮንቶስ 6: 2** ላይ ነገ እንኳን በጣም የረፈደ ሊሆን እንደሚችል ተመልከቱ። በተጨማሪም ልክ በ70 ዓ.ም በቲቶ ግዛት ስር እንደሆኑት እንዴት በዚህ አለም ላይም ፍርድ እንደሚወድቅ እናም ለጌታ ኢየሱስ ጊዜ የሌላቸው እንደሚጠፉ አስቡ። | ስለ ኢየሱስ ህይወት በሚያወራው ክፍል ለይ በማተኮር ይህን ጥናት ከልሱ።እየሩሳሌም የሀይማኖትና የፖለቲካ ስልጣን ማዕከል እንዲሁም ደግሞ አይሁድና ሮማውያን ለሆኑ አገር ገዢዎች ቤት ነበረች። አብዛኛዎቹ ዋና ዋና የሚባሉት የኢየሱስ የህይወት ገጠመኞች ስቅለትና ሞቱን ጨምሮ በዚህ ስፍራ ነበር የተከናወነው።የመጨረሻ ሳምንቱንም ሙሉ እዚሁ ነው ያሳለፈው። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ከኃጢአት መመለስና ለመዳን በጌታ ኢየሱስ ማመን ምን ማለት እንደሆነ አስቡ።<br>2. ቁልፍ ጥቅሱ የሚያመለክተው ጌታ ኢየሱስ “የእግዚአብሔር ልጅ” መሆኑን የተቀበሉ ሰዎችን ነው። ጌታ ኢየሱስን የተቀበሉ ሰዎች የሚታወቁባቸውን ሌሎች ቃላት አስቡ።(ምሳሌ-ክርስቲያን. . .) | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ዘላለማዊ ህይወት እድሉ በተሰጣቸው ጊዜ ለሚቀበሉት ሰዎች አሁንም አለ።<br>2. የእኛን ህይወት ጌታ ሊጠቀምበት የሚችልባቸውን መንገዶች አስቡ።<br>3. ***በዘካሪያስ 9:9*** ላይ የተነገረው ትንቢት እንደተፈፀመ ሁሉ ስለ ጌታ ዳግም መምጣት የተነገሩት ትንቢቶችም ይፈፀማሉ። |

| | ለ4 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – ጌታ ኢየሱስ<br>ርእስ – ‘መሞት’ | ለ4 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – ጌታ ኢየሱስ<br>ርእስ – የእርሱ ሞት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 23: 1-26 እና 32-46***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 23: 33***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ኢየሱስ የሞተው ኃጢአታችን ይቅር እንዲባል ነው።<br>2. ወደ መንግስተ ሰማይ ለመድረስ ከኃጢአታችን መመለስና በጌታ ኢየሱስ ማመን ይኖርብናል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 23: 32-56***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 15: 13,14***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ወደ መንግስተ ሰማይ ለመድረስ ኃጢአተኞች መሆናችንንና የእግዚአብሔር ቅጣት እንደሚገባን ማወቅ አለብን።<br>2. ከዚያም ጌታ ኢየሱስ ምንም ኃጢአት እንዳላደረገና በእኛ ቦታ ሆኖ ቅጣታችንን እንደወሰደ ማመን ይኖርብናል። |
| **አስተዋውቂ** | ተማሪዎችን ስለ ፋሲካ ምንነት ምን እንደሚረዱ በመጠየቅ ትምህርቱን አስተዋውቁ።ይህ ትምህርት ስለ መጀመሪያው ፋሲካ እንደሚናገር አስረዱ።<br>ይህ ትምህርት እንዴት ሁሉም ሰው ወደ መንግስተ ሰማይ እንደማይገባ እንደሚያሳይ አብራሩ።ከጌታ ኢየሱስ ጎን ከነበሩት ውስጥ አንዱ ሌባ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄዷል አንዱ ግን አልሄደም። | እስከመስቀል ድረስ እስኪደርስ የለውን አካሄድ መታሰሩን፣ስቃዩንና ወደ ጎልጎታ ሲሄድ ያለውን ነገር እያንዳንዱን አብራሩ።<br>ይህ ጥናት መዳን ንስሀ በመግባትና በእምነት ለይ የተመሰረተ እንደሆነ በተጨማሪም ደግሞ ንስሀ የገባው ሌባ ወደ መንግስተ ሰማይ መሄዱንና ንስሀ ያልገባው ግን አለመሄዱን አብራሩ። |
| **አጠናቂ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን** ***ታሪክ*** **አቅርቡ**<br>***ማብራራታ*** **እና ማስረዳት፡**<br>1. ጲላጦስ ኢየሱስ ላይ ምንም ጥፋት አላገኘም ነበር ነገር ግን ሰዉን ለማስደሰት ብሎ እንዲገደል አዘዘ። ***(ከቁጥር 1-7፣ 13-25)***<br>2. ጲላጦስና ሄሮድስ ጠላቶች ቢሆኑም እንኳን ጓደኛሞች በመሆንና በኢየሱስ ላይ በማበር በአንድ ወገን ነበሩ። ***(ቁጥር 12)***<br>3. የመሰዋቱ ሰአታት (ከ3-9)-ኢየሱስ መሀል ሆኖ ሌቦቹ በሁለቱም በኩል ***በኢሳያስ 53: 12*** ያለው ትንቢት መፈፀሙን ያሳያል።<br>4. ሁለት ሌቦች ነበሩ ***(ከቁጥር 39-43)*** ነገር ግን አንዱ ብቻ ነው ወደ መንግስተ ሰማይ የሄደው። ሀሳባችሁን ***ቁጥር 43*** ለይ አድርጉ-“ዛሬ” – በምን ፍጥነት! “ከእኔ ጋር” – ምን አይነት አብሮነት! “በመንግስተ ሰማይ” – ምን አይነት ደስታ!<br>5. ሶስት የጨለማ ሰአታት ***(ከቁጥር 44-46***) እና የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ለሁለት መቀደድ ጌታ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መድረሻው መንገድ መሆኑን አሳይቷል ***ዕብራውያን 10: 19-20***።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ኢየሱስ በጲላጦስና በሄሮድስ ፊት ፣ ኢየሱስ ተሰቀለ ፣ኢየሱስ ሞተ።** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን** ***ታሪክ*** **አቅርቡ**<br>***ማብራራታ*** **እና ማስረዳት፡**<br>1. የተሰዋበት ሰአት ***ኢሳያስ 53: 12*** መፈፀሙን አሳይቷል (ከ3-6ሰአት)።<br>2. ንስሀ የገባው ሌባ ታሪክ፡ ***(23: 43)*** መዳን ንስሀ በመግባትና በእምነት ለይ ብቻ የተመሰረተ እንደሆነ ያሳየናል።ይህ ሰው ወደ መንግስተ ሰማይ ሄዷል ነገር ግን ተጠምቆም ሆነ ምንም አይነት ስርአት ፈጽሞ አያውቅም።<br>3. ሁለቱ ሌቦች የተለያዩ ሰዎችን ነው የሚወክሉት-ጌታ ኢየሱስን የሚወዱትንና የእርሱ ጠላቶች የሆኑትን።<br>4. ለሶስት ሰአታት ጨለማ በሆነበት ጊዜ (***ከቁጥር 44-46)*** ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት እየወሰደ ነበር እናም በሞቱ ሁሉም ወደ እግዚአብሔር በእምነት ይመጣበት ዘንድ የመድረሻው መንገድ ተከፍቷል።<br>5. ታሪኩ የሚያሳየው ***(ከቁጥር 50-56)*** ለኢየሱስ በተደረገው የክብር አቀባበር እንደ ሴቶቹ ሁሉ ዮሴፍ የተደበቀ ደቀመዝሙር ቢሆንም እንኳን የጌታ ኢየሱስ ታማኝ ጓደኛ እንደነበር ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ኢየሱስ ተሰቀለ ፣ ኢየሱስ ሞተ።** |
| **እዲታወስ** | ጌታ ኢየሱስ ከመሞቱ ከ100 አመታቶች በፊት የተፃፈውን ***ኢሳያስ 53: 12*** በማንበብ ትምህርቱን ከልሱ እና የመጽሐፍ ቅዱስን ዋና ትኩረት ተመልከቱ።<br>በቡድን በመሆን በመስቀል ለይ የነበረውን ሁኔታ የሚያሳዩ አንዳንድ የጋዜጣ ርእሶችን ፃፉ። | ኢየሱስ ከመሞቱ ከ100 አመታቶች በፊት የተፃፈውን ***ኢሳያስ 53*** እንዲያነቡ ተማሪዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ከልሱ እና ***ከሉቃስ 23: 32-56*** ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል አስረዱ።መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መፃፉ ጎልቶ መታየት አለበት።<br>በቡድን በመሆን ***በኢሳያስ 53*** ለይ ከተጠቀሱት አንዳንድ ትንቢቶች መሀል መስቀሉ ለይ የተፈፀሙትን ትንቢቶች ዝርዝር ስሩ። |
| **የተግባር** ***ሥራ*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ኃጢአታችን ይቅር መባሉን እንዴት ነው እርግጠኛ መሆን የምንችለው?<br>2. ሁላችንም በየትኛው ጎን እንዳለን የሚለይ ፈተና ይገጥመናል-ጌታ ኢየሱስን በሚወዱት ጎን ወይንም ደሞ ጠላቶቹ በሆኑት ጎን።<br>3. ሁሉም ሰው መንግስተ ሰማይ ይገባል ለሚል ሰው እንዴት አይነት ምላሽ ነው የምትሰጡት? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ሁላችንም የኢየሱስ ጓደኛ ወይንም ደግሞ ጠላት መሆናችንን የሚለይ ፈተና ይገጥመናል።<br>2. ጌታ ኢየሱስን የምንወደው ከሆነ ልክ እንደ ዮሴፍ የምናሳይበትን መንገድ እንፈልጋለን። እንዴት ማሳየት እንችላለን?<br>3. ሁሉም ሰው መንግስተ ሰማይ ይገባል ለሚል ሰው እንዴት አይነት ምላሽ ነው የምትሰጡት? |

| | ለ4 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – ጌታ ኢየሱስ<br>ርእስ – መነሳት | ለ4- ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – ጌታ ኢየሱስ<br>ርእስ – የእርሱ ትንሳኤ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዮሐንስ 20: 1-18***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሮሜ 10: 9***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. በመቃብር ውስጥ ለሶስት ቀናት ከቆየ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ተነሳ።<br>2. መግደላዊት ማርያም ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅሯን አሳየች። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 8: 1-3፣ ዮሐንስ 20: 1-18***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሮሜ 10: 9***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስ ሞቶ ሲነሳ ሞትን አሸነፈ።<br>2. መግደላዊት ማርያም የተሰጠች የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ነበረች። |
| **አስተዋውቁ** | የ"ትንሳኤ"ን ትርጉም አብራሩና ጌታ ኢየሱስ ከሞት ያስነሳቸውን ማንኛውንም አይነት ሰዎችነ (አልዓዛር - ***ዮሐንስ 11: 44***፣የኢያኢሮስ ልጅ - ***ሉቃስ 8: 55***) ተማሪዎች እንዲለዩ ጠይቋቸው። የትንሳኤ ሀይል የኢየሱስ መሆኑን ሀሳብ ውስጥ አስገቡ። | የትንሳኤው ሀይል የጌታ ኢየሱስ ስለመሆኑ አብራሩና እርሱ ከሞት ያስነሳቸውንም ሰዎች (አልዓዛር - ***ዮሐንስ 11: 44***፣የኢያኢሮስ ልጅ - ***ሉቃስ 8: 55***) ለዩ። በተጨማሪም እንዴት ጌታ ኢየሱስን አምነው የሞቱ ሰዎች ትንሳኤን እንደሚያገኙ አስምሩበት። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br><br>***ማብራራታ* እና ማስረዳት፡**<br>1. መግደላዊት ማርያም፣ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ለትንሳኤው ማስረጃ የሚሆንን ነገር አይተዋል-ባዶ መቃብር።<br>2. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ወደ ቤት ሄዱ መግደላዊት ማርያም ግን ብቻዋን ከመቃብሩ ውጪ ነቅታ ቆየች።<br>3. ጌታ ኢየሱስ ለፍቅሯ ምላሽን ለመስጠት በአካል ተገለጠላት እናም ወደ መንግስተ ሰማይም ሲሄድ በአማኞች ልብ ውስጥ እንደሚኖር መንፈሱን እንደሚልክም አስረዳት።<br>4. ሄዳ ኢየሱስ በህይወት እንዳለና በገሊላም እርሱን ማግኘት እንዳለባቸው ለደቀመዝሙሩ እንድትናገር ላካት።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – ኢየሱስ ከሙታን ተነሳ።** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br><br>***ማብራራታ* እና ማስረዳት፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስን በነበረበት ዘመን ተገዛችለት እናም ባዶው መቃብር ጋር አንደኛ በመገኘት ታማኝነቷን አሳየች።<br>2. መግደላዊት ማርያም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለትንሳኤው ማስረጃ የሚሆንን ነገር አይተው ነበር በተጨማሪም ንፁህና ተስተካክሎ የተቀመጠውን ኢየሱስ ተገንዞበት የነበረውንም ጨርቅ አይተዋል። ይህ ደግሞ የኢየሱስ አስክሬን ተሰርቆ ነበር የሚለውን ሀሳብ ስህተት መሆኑን በማስረዳት የጌታ መነሳት የተዘጋጀና በእርጋታ የተፈፀመ መሆኑን ያሳያል።<br>3. ጌታ ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ለፍቅሯ ምላሽን ለመስጠት በአካል ተገለጠላት እናም ወደ መንግስተ ሰማይም ሲሄድ በአማኞች ልብ ውስጥ እንደኖር መንፈሱን እንደሚልክም አስረዳት።<br>4. ሄዳ ኢየሱስ በህይወት እንዳለና በገሊላም እርሱን ማግኘት እንዳለባቸው ለደቀመዝሙሩ እንድትናገር ላካት።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ኢየሱስ ከሙታን ተነሳ።** |
| **እዲታወስ** | ይህን ትምህርት ኢየሱስ ትንሳኤውን አስቀድሞ ከተናገረበት አዲስ ኪዳን ለይ ካሉትና ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ማጣቀሻ ነጥቦች ጋር አያይዙ።የትንሳኤን ምንነትና አስፈላጊነት አብራሩ።<br>• ***ማቴዎስ 16: 21, 17:23፣ 20:19***<br>• ***ሉቃስ 18: 33፣ 24: 7***<br>• ***1 ቆሮንቶስ 15: 3-4*** | ይህን ትምህርት ***ከ1 ቆሮንቶስ 15: 3-8, 12-20*** ጋር አገናኙና ***ቁጥር 4*** እንዴት ***ኢሳያስ 53: 9*** እና ***መዝሙር 16: 9-10*** እደሚያመለክት አሳዩ።<br>ከትንሳኤው በኋላ ኢየሱስን ስላዩት ብዙ አይነት ሰዎች (***ከቁጥር 5-8)*** እና ትንሳኤው ለምን ጠቃሚ እንደሆነ አብራሩ። ***(ቁጥር 20)*** |
| **የተግባር *ሥራ*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ተማሪዎች ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው እንወደዋለን የማለታቸው ጥቅም።<br>2. እኛ ለእርሱ ያለን ፍቅር ህይወታችን ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር አስቡ።<br>3. በተጨማሪም ከዚህ ትምህርት ትንሳኤው እርግጥ መሆኑን መማር አስፈላጊ ነው። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ከጌታ ኢየሱስ ጋር የግል ግንኙነትና ለእርሱ ያለን ፍቅር ያለውን አስፈላጊነት አስቡ።<br>2. ትንሳኤ ለክርስትና እምነት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው ምክንያቱም ኢየሱስ ከሙታን ባይነሳ ኖሮ ሞቱ በከንቱ ይሆን ነበር።እኛም በመንግስተ ሰማይ ለዘላለም ለመኖር ምንም ተስፋ አይኖረንም ነበር። |

| | ለ4 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – ጌታ ኢየሱስ<br>ርእስ – ‘መሄድ’ | ለ4 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – ጌታ ኢየሱስ<br>ርእስ – ማረጉ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዮሐንስ 20: 19-29፣ ሉቃስ 24: 50-53***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሉቃስ 24: 51***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስ በቃሉ በኩል የሆነ ነገር በሚናገርበት ጊዜ የምናስደስተው ቃሉን በማመን ነው።<br>2. የዮሐንስ ወንጌል አላማ የሚያነቡት እንዲያምኑና ዘላለማዊ ህይወትን እንዲያገኙ ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሉቃስ 24: 45-53፣ ሐዋ.ስራ 1: 1-12***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሉቃስ 24: 51***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጌታ ኢየሱስ የእርሱ የሆኑት በምድር ለይ ምስክሮች እንዲሆኑት ይፈልጋል።<br>2. አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ የእርሱ የሆኑትን ወደ መንግስተ ሰማይ ለመውሰድ ወደ ምድር ይመጣል። |
| **አስተዋውቁ** | እንዴት የማናየውንና የማንዳስሰውን ነገር እንደምናምን አሳማኝ የሆኑ ምሳሌዎች በማቅረብ አብራሩ።የክርስትና እምነት እንዴት በማየት ለይ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃልና ጌታ ኢየሱስን በማመን ለይ የተመሰረተ እንደሆነ አስረዱ። | የምንወዳቸው ሰዎችን የመጨረሻ ቃል በተለይም ሊሞቱ ሲሉ የሚናገሩትን ምን ያህል እንደምናከብር አስረዱ።በታሪክ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ታላላቅ ሰዎች ከመሞታቸው በፊት የተናገሩትን የመጨረሻ ቃል አስቡና ከጌታ ኢየሱስ የመጨረሻ ቃል ጋር አገናኙ።<br>***(ሐዋ. ስራ 1: 8-9)*** |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. የጌታ ኢየሱስን ለደቀመዝሙሩ መገለጥ አብራሩና የተናገረውን ቃልም አስተውሉ፡ “ሰላም ለእናንተ ይሁን”። ***(ቁጥር 21)*** በኢየሱስ ሞት አማካኝነት አማኝ የሆኑ ሰዎች በእምነት በኩል እውነተኛ ሰላም እንዳላቸው አብራሩ።<br>2. ኢየሱስ እምነት ለጎደለው ቶማስ በእርጋታ በመመለስ ትንሳኤ የሆነው እራሱ ራሱ ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ አሳመነው።<br>3. ቶማስ በእምነት ቃላትና በመሰጠት ምላሽ ሰጠ።<br>4. ጌታ ኢየሱስ ያረገው ከትንሳኤው ከአርባ ቀናት በኋላ በደብረዘይት ተራራ ለይ ነበር ከዚያም ደቀመዝሩ ስለ ትንሳኤውና ስለ ዳግም መምጣቱ ለማክበርና እግዚአብሔርን ለማመስገን ወደ ቤተ-መቅደሱ ተመለሱ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – ኢየሱስ ለደቀመዝሙሩ ተገለጠ ፣ኢየሱስ ለቶማስ ተገለጠ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ጌታ በእየሩሳሌም፣በፊልስጤምና በአለም ዙሪያ ሁሉ ምስክር እንዲሆኑት ***(ሐዋ. ስራ 1: 8)*** ደቀመዝሙሩን አዘዘ።<br>2. ጌታ ኢየሱስ በደብረዘይት ተራራ ለይ አረገ ***(ቁጥር 12)*** እና የሚመለሰውም በደብረዘይት ተራራ ለይ ነው። ***(ዘካሪያስ 14: 4)***<br>3. ያረገው በአካል እና እየታየ ነበር።ሲመለስም እንዲሁ በአካልና (***ሚልኪያስ 3: 1)*** እየታየ ነው። ***(ማቴዎስ 24: 30)***<br>4. ሲያርግ በሀይልና በክብር ደመና ተቀበለው ሲመለስም እንዲሁ በደመና በክብርና በሞገስ ይመጣል።(***ማቴዎስ 24: 30)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ኢየሱስ ወደ ሰማይ አረገ** |
| **እዲታወስ** | ቁልፍ ጥቅሱን አጥኑና ትምህርቱን እንዴት እንደሚያጠቃልል አብራሩ።ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት ቃል የተገባላቸው እንዲፈፀም ደቀመዝሩ እየጠበቁ እንደነበር ተማሪዎችን አስታውሱ። ***( ሉቃስ 24: 49)*** | ከላይ የተጠቀሱትን አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ ነጥቦችን ተመልከቱና የጌታን ወደ መንግስተ ሰማይ ማረግ ከዳግም ወደ ምድር መምጣቱ ጋር አወዳድሩ አነፃጽሩ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br><br>1. ጌታ ኢየሱስን ባናየውም እንኳን ለመዳን እንዴት ነው ልናምነው የምንችለው?<br>2. ጌታ ኢየሱስ ከሄደ በኋላ ለእርሱ እንዲሰሩለት ደቀመዝሙሩን አበረታታ።አሁን እኛ ምን ስራ ልንሰራለት እንችላለን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br><br>1. በጌታ ኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች እንዴት ነው በቤት፣በት/ቤት ወይንም በጓደኞቻቸው መሀል ስለ እርሱ ሊመሰክሩ የሚችሉት?<br>2. ሚሲዮናዊ ለመሆን መኖሪያቸውን ትተው ወደ ሌላ ቦታ ስለሚሄዱ ሰዎች አስቡ።<br>3. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ምስክርነት እንዳለው እውነታ ትንሳኤውን አስቡ። |

| | **ለ4 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 4 – ጌታ ኢየሱስ**<br>**ርእስ – 'መመለስ'** | **ለ4 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 4 – ጌታ ኢየሱስ**<br>**ርእስ – ዳግመኛ መምጣቱ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሐዋ. ስራ 1: 4፣ 8-12***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሐዋ. ስራ 1: 11***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ወንጌሉን ስንመሰክርም ሆነ ስንሰብክ የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ያስፈልጋል።<br>2. ወደ ሰማይ ያረገው ጌታ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ለመኖር ዝግጁ የሆኑትን ወደ መንግስተ ሰማይ ለመውሰድ ተመልሶ ወደ ምድር ይመጣል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዮሐንስ 14: 1-6፣ ሐዋ. ስራ 1: 9-11***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***1 ተሰሎንቄ 4: 16-17***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ቀኑና ጊዜው ባይታወቅም እንኳን የጌታ ወደ ምድር ዳግም መምጣት በእርግጥ ሊሆን ያለ ነገር ነው ።<br>2. በዳግም ምጽአቱ ጊዜ በጌታ ሆነው ያንቀላፉት ይነሳሉ እና በጊዜው በህይወት ካሉ ክርስቲያኖች ጋር ወደ መንግስተ ሰማይ ይወሰዳሉ። |
| **አስተዋውቁ** | ምስክር መሆን ስለሚችል ሰው አውሩ ለተፈጠረ አደጋ ሊሆን ይችላል። ስለተፈጠረው ነገር በትክክል ያየ እና የሰማ ሰው መሆን አለበት።ደቀመዝሙሩ ራሳቸው ከጌታ ኢየሱስ ጋር ካሳለፉት ህይወት ያወራሉ።<br>ለጌታ ኢየሱስ ምስክር ለመሆን ደቀመዝሙሩ የተቀበሉት ሀይል እኛ አሁን ከኃጢአታችን ተመልሰን ጌታ ኢየሱስ ኃጢአታችንን ለመውሰድ በመስቀል ለይ የሰራልንን ስራ ስናምን የምንቀበለው ሀይል መሆኑን አስቡ።እኛ ምስክር መሆን እንችላለን መሆንም አለብን። | በብሉይ ኪዳን ጌታ ሰው ሆኖ ወደ ምድር መምጣት የተነገሩት ትንቢቶች በሙሉ እንደተፈፀሙ ሁሉ ስለ ዳግም መምጣቱ የተነገሩት ትንቢቶችም ሁሉ እንደሚፈፀሙ ተማሪዎችን አስታውሱ።<br>የምንወደው ሰው እርቆ ሲሄድ መመለሱን ምን ያህል እንደምንናፍቅ እና ደግሞ ጌታ ኢየሱስን የሚያምኑ ሰዎች የእርሱን መምጣት መናፈቅ እንዳለባቸው ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ። ***ቲቶ 2: 13ን*** ተመልከቱ። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ጌታ ደቀመዝሙሩን መጀመሪያ በእየሩሳሌም ከዚያም ደግሞ በሰማሪያ ምድርና በመጨረሻም በአለም ሁሉ ምስክሮች እንዲሆኑለት አዘዛቸው። ***(ሐዋ. ስራ 1: 8)***<br>2. መቃብሩ ጋር የመጡት ሴቶች ያገኟቸው "የሚያበራ ልብስ ያደረጉት ሁለቱ ሰዎች" ***(ሉቃስ 24: 4)*** መቃብሩ ባዶ እንደሆነና ጌታ ኢየሱስም ከሙታን እንደተነሳ ነገሯቸው።እነዚህ መላእክቶች ራሳቸው በሰው ተመስለው ለደቀመዝሙሩ ስለ ኢየሱስ ዳግም መምጣት ነገሯቸው። ***(ሐዋ. ስራ 1: 10-11)***<br>3. ተመልሶ መምጣቱ ከእርገቱ ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው የሚሆነው።<br>4. ተመልሶ የሚመጣበት ጊዜ አይታወቅም ስለዚህም ዝግጁ ሆነን መጠበቃችን አስፈላጊ ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል ኢየሱስ ወደ ሰማይ አረገ።** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. "የሚያበራ ልብስ ያደረጉት ሁለቱ ሰዎች" ***(ሐዋ. ስራ 1: 10-11)*** ለደቀመዝሙሩ የጌታን ዳግም ወደ ምድር መምጣት ነገሯቸው። እነዚህ የመላእክትን ማንነት የያዙ ሰዎች ***በሉቃስ 24: 4*** መቃብሩ ጋር ለነበሩት ሴቶች ስለ ትንሳኤው የተናገሩት ራሳቸው መሆናቸውን አገናኙ።<br>2. ***በዮሐንስ 14: 3*** ላይ ያለውን የጌታን ቃል ***ከሐዋ. ስራ 1: 11*** ጋር አወዳድሩና የጥቅሶቹን እርግጠኛነት እና ዋና ሀሳብ አብራሩ።<br>3. ***1 ተሰሎንቄ 4: 16-17ን*** አንብቡና ስለ ዳግም መምጣቱ ጳውሎስ የነበረውን በጣም ልዩ የሆነ መግለጥ አብራሩ።ቀጥሎ በተፃፉት መሰረት አብራሩ፡<br>የሚሰማ ድምጽ -ጩኸትና መለከት (ጡሩንባ)<br>የሚታይ እይታ -ራሱ ጌታን<br>የሚሰማን ተአምራት-መነጠቅ<br>የምንደሰትበት ግንኙነት-"ጌታን በአየር መገናኘት"<br>የሚሰማን ምቾት-"ከጌታ ጋር" ለዘለአለም መኖር።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:የሚሆን ስዕል የለም** |
| **እዲታወስ** | ቀጥሎ የተፃፉትን ጥቅሶች ተመልከቱና ሌባ መቼ እንደሚመጣ ማንም አያውቅምና "እንደ ሌባ በሌሊት" እንደሚመጣ እንደተናገረ አሳዩ ።ስለዚህም በእርሱ የማመናችን ጥቅም ለመዳናችንና ተመልሶ ሲመጣ ተዘጋጅተን እንድንጠብቀው ነው። ***ማቴዎስ 24: 44፣ ሉቃስ 12: 20*** | ዳግመኛ መምጣቱ ለዳኑትና እርሱን ለመገናኘት ዝግጁ ለሆኑ ሰዎች ምንም አያስፈራም።ክርስቲያኖች የእርሱን መገለጥ መጠባበቅና እርሱን ለማስደሰት በቅድስና መኖር እንዳለባቸውመጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ***ቲቶ 2: 11-14ን እና 1 ዮሐንስ 3: 2-3ን*** ተመልከቱ። |
| ***የተግባር ሥራ*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ጌታ ኢየሱስ አሁን ቢመጣ ሁሉም ወደ መንግስተ ሰማይ ለመሄድ ዝግጁ ስለ መሆናቸው ማሰብ አለባቸው።<br>2. ለመንግስተ ሰማይ ለመዘጋጀት ብዙ ጊዜ አለ ብሎ ለሚያስብ ሰው ስለ ዳግም መምጣቱ እንደተማራችሁት በማሰብ ምንድነው መልሳችሁ የሚሆነው?<br>3. ለመንግስተ ሰማይ ለመዘጋጀት የትኛው ጊዜ ነው ምርጥ? ***2 ቆሮንቶስ 6: 2ን*** ተመልከቱ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. የጌታ ዳግም መምጣት በመቀረቡ ውስጥ ሆነው አማኞች የጽድቅን ህይወት መኖርና እና ሲመጣም ለእርሱ ታማኝ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል።ይህ ምን ማለት ነው?<br>2. የማያምኑ ሰዎች በዳግም ምጽአቱ ጊዜ ወደኋላ ይተዋሉ።እንደ ክርስቲያን ለእነርሱ ከመመስከር አንፃር ይህ አሳዛኝ እውነታ እንዴት ነው ሊያነሳሳን የሚገባው? |

| | **ለ5 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 1 – የጌታ ባሪያዎች**<br>**ርእስ – በእግዚአብሔር የተዘጋጀ** | **ለ5 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 1 – የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች**<br>**ርእስ – እስጢፋኖስ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ሐዋ.ስራ 1: 7-9፣ ሐዋ.ስራ 2: 1-13***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ዮሐንስ 14: 16-17***<br>**የምንማረው፡**<br>1. በቤተክስቲያን የመጀመሪያ ቀናቶች ጌታ ሐዋርያቱን በአካባቢያቸውና በአለም ዙሪያ ሁሉ ወንጌልን እንዲሰብኩ አዘዛቸው።<br>2. መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያቶቹ ልብ ውስጥ እንደነበረው ሁሉ በጌታ በኢየሱስ የሚያምኑትም የእርሱ መገኘትና በክርስትና ህይወታቸው የሚረዳቸው ሀይሉ ይኖራቸዋል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ሐዋ.ስራ 6: 1-15፣ 7: 54-60***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ሐዋ.ስራ 6: 8***<br>**የምንማረው፡**<br>1. የእስጢፋኖስ አይነት ብቃት ያላቸው ሰዎች ናቸው ይህን አለም ለእግዚአብሔር የሚለውጡት።<br>2. ልክ እንደ እስጢፋኖስ ያሉ እውነተኛ አማኞች ብቻ ናቸው የወንጌልን እውነት ሊያውጁ የሚችሉት እናም የበለጠ የሚጨነቁት ደግሞ ሰው ስለሚላቸው ወይም ስለሚያደርግባቸው ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር ስለሚለው ነገር ነው። |
| **አስተዋውቁ** | ጌታ ኢየሱስ ካረገ በኋላና በበዓለ ሀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ለደቀዝሙሩ እንዴት ሊሆን እንደሚችል እንዲያስቡ ተማሪዎችን ጠይቁ።<br>የሀዋርያቶቹ ስራ በሁለት አይነት እንዴት እንደሚከፈል አብራሩ፡<br>1. ያረገው ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምድር እርሱን ባመኑት በኩል በመንፈሱ አማካኝነት ስራ እየሰራ ነው።<br>2. ይህ መጽሐፍ ሲፃፍ የመልእክቱን ፍሬ ነጥብ የመሰረተው የጌታ ኢየሱስ ትንሳኤ እና ወደ መንግስተ ሰማይ ማረጉ ነው። 60-70 ዓ.ም። | መሰዋዕት ምን ማለት እንደሆነ አብራሩና በዚህ ዘመን ካሉት ውስጥ ምሳሌዎችን አስቡ።<br>በክርስትና የመጀመርያ ቀናቶች ውስጥ የሃይማኖት መሪዎች በመንግስቱ ውስጥ ትልቅ ተጽኖ ያሳድሩ እንደነበር እና ክርስቲያኖችም ለእነርሱ ተቃውሞ ዝግጁ እንደነበሩ እና ሁሌም ምላሽ የሚሰጡት በኩራት እንደነበር አብራሩ። የሰዎቹ ህግ ከእግዚአብሔር ህግ ጋር ካልተቃረነ በቀር ክርስቲያኖቹ በጊዜው የነበረውን መንግስት ያከብሩና ይታዘዙ ነበር። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ***ሐዋ.ስራ 1: 8*** በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቁልፍ ጥቅስ ነው የወንጌልን ስርጭት በተመለከተ ሙሉ የሐዋርያት ስራ የተመሰረተው በዚሁ ላይ ነው።<br>በእየሩሳሌም ምስክሮች - ***ምእራፍ 1-7***<br>በአይሁድ ምስክሮች - ***ምእራፍ 8: 1-4***<br>በሰማሪያ ምስክሮች - ***ምእራፍ 8: 5-25***<br>በአለም ሁሉ ምስክሮች - ***ምእራፍ 8: 26***<br>2. የበዓለ ሀምሳ ቀን ***(2: 1)*** መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ በዘላቂነት መኖር የጀመረበት ቀን ነው ለመቆየት ነበር የመጣው። እነሱም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር ***(2: 4)።*** በጌታ ኢየሱስ ስናምን መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ይኖራል ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብ፣ በፀሎት ጊዜ ማሳለፍና ለጌታ በታዛዥነት መኖር አለብን።<br>3. ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በጨረሰው ስራ ፍፁም የሆነ መሰረት ነው የጣለው እናም አሁን ምስክሮች እንዲሆኑ እና የሞቱን፣የትንሳኤውንና የመዳንን መልካም ዜና ለሁሉም እንዲያሰራጩ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለአማኞች ሀይል ይሰጣል። መንፈስ ቅዱስ በቁልፍ ጥቅሱ ***ዮሐንስ 14: 16*** ላይ "አጽናኝ" ተብሏል።ይህ ጌታ ኢየሱስ ጠበቃችናና ረዳታችን መሆኑንም ያሳየናል።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል - የበአለ ሀምሳ ቀን** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. እስጢፋኖስ በክርስቲያን ህይወት ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ ብቃቶች ነበሩት፡ ታማኝነት፣በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ፣በእምነት እና በሀይል የተሞላ፣ጥበበኛ እና ጌታ ኢየሱስን የሚያገለግል። ***( ሐዋ.ስራ 6: 3፣5 እና 8ን ተመልከቱ)***<br>2. በእስጢፋኖስ ሀይል የተሞላ አገልግሎት ላይ በእየሩሳሌምና በአቅራቢያው ባሉ ከተሞች በምኩራብ ውስጥ ከሚሰባሰቡ አይሁዶች ተቃውሞ ተነሳበት።ምንም ቢሆን ግን በአይሁድ ፍርድ ቤት ሲቆም የውሸት ክስ ነበር የሰሙት፤የኢየሱስ ክብር በእስጢፋኖስ ፊት ላይ በርቶ አዩ (***ሐዋ.ስራ 6: 15)*** እስጢፋኖስ በልበ ሙሉነት ምላሽ ሰጠ***(ሐዋ.ስራ 7: 1-53)*** እና መንፈስ ቅዱስንና የጌታ ኢየሱስንም ስቅለት ስለተቃወሙ የአይሁድ መሪዎችን በመውቀስ የንግግር ናዳ አወረደባቸው።<br>3. እስጢፋኖስ ህይወቱ አደጋ ውስጥ መሆኑን ያውቅ ነበር ነገር ግን ጌታውን ከሚከዳ ይልቅ ሞትን ይመርጣል።ልክ "የሰማያት ደጆች ተከፍተው" ***(ሐዋ.ስራ 7: 56***) አይቶ በተናገረበት ቅጽበት ህዝቡ ጎትተው ከከተማ ውጪ አወጡት እናም እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ወገሩት።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – እስጢፋኖስ ተወገረ** |
| **እዲታወስ** | የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ፀሀፊ ዶ/ር ሉቃስ የሚጀምረው ***በሐዋ.ስራ 1: 1*** "ኢየሱስ ያደረገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ" በማለት ነው። ***በሐዋ.ስራ 28: 31*** ለይም ጳውሎስ የወንጌሉን የምስራች በመናገር ለይ ነበር።ይህን አስተውሉ "የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ አሁንም ይቀጥላል - ጌታ የሚየምኑበትን ሰዎች ለመውሰድ እስኪመለስ ድረስ የወንጌል ስራ አያልቅም።" | እነዚህ ጥቅሶች ትምህርቱን እንዴት እንደሚያጠቃልሉ አብራሩ።<br>1. ***2 ጢሞቴዎስ 2: 3*** – "እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ መከራን ተቀበል"<br>2. ***1 ጴጥሮስ 4: 14*** –"ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ" |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. እንደ አማኝ በውስጣችን መንፈስ ቅዱስ ይኖራል።"በመንፈሱ መሞላት" የእኛ ሀላፊነት ነው። ***ኤፌሶን 5: 18ን*** አንብቡ።<br>2. እነዚህን ትምህርቶች መማራችሁ መጽሐፍ ቅዱስ እንድታነቡና እንድፀልዩ ሊያበረታታችሁ ይገባል።ያነበባችሁትንና በእለት ተእለት ህይወታችሁ ጌታ የሚሰጣችሁን እገዛ አስቀምጡ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ልክ እስጢፋኖስ በጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በማመኑ ምክንያት እንደተወገረው ሁሉ ዛሬም ብዙ ክርስቲያኖችም በተለያዩ ሀገራት ውስጥ እየተሰቃዩና እየተገደሉ ይገኛሉ።<br>2. በህይወታችን በማንኛውም አይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ለጌታ ኢየሱስ ታማኝ እንድንሆንለት በፀሎታችን እርሱን መጠየቅ አለብን። |

| | **ለ5 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 2 – የጌታ ሰራተኞች**<br>**ርእስ – ለመሞት የተዘጋጀ!** | **ለ5 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 2 – የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች**<br>**ርእስ – ፊሊጶስ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሐዋ. ስራ 6: 1-5፣ 8-15፤ 7: 54-60***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ 5: 44***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. እስጢፋኖስ የእግዚአብሔር መጠቀሚያ ከመሆኑ በፊት ታላቅ ድንቅና ተአምራትም ከማድረጉ በፊት ***(ሐዋ.ስራ 6: 8)*** የማእዱን አገልግሎት በማስተናገድ እንደታየው ***(ሐዋ.ስራ 6: 2)*** ትናንሽ በሆኑት ነገሮች ታማኝ ነበር።<br>2. እስጢፋኖስ ታማኝና ነፍሱን ስለ ወንጌል ሊሰጥ የተዘጋጀ እንከን የሌለበት ሰው በመሆኑ ልክ እንደ ጌታ ኢየሱስ ነበር። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሐዋ.ስራ 6: 5፤ 8: 4-17፣ 8: 26-40***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሐዋ.ስራ 8: 35***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ፊሊጶስ በሰማሪያ የተነሳውን የወንጌል እሳት ትቶ ለአንድ የተቸገረ ሰው ሲል ወደ ጋዛ ለመሄድ ፈቃደኛ የሆነ ስኬታማ የወንጌል ሰባኪ ነበር ።<br>2. ኢትዮጲያዊው ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ ካመነ በኋላ በጥምቀት ጌታን ሊታዘዝ ጓጉቶ ነበር እናም ወደ ቤቱ ሲመለስ በልቡ ትልቅ ደስታ ሞልቷል። |
| **አስተዋውቁ** | ለእምነታችሁ መሰዋት ምን ማለት እንደሆነ አስቡ እና በዚህ ዘመን ካሉ ምሳሌዎች ውስጥ ጥቀሱ።<br>የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ወንጌልን ይዘው ወደፊት እንደተራመዱ እንዴት ከመንግስትና ከሀይማኖት መሪዎች ተቃውሞ እንደገጠማቸው አብራሩ።መሪዎቻቸውን ቢያከብሩና ቢታዘዙም ግን የሰዎቹን ህግ ከእግዚአብሔር ህግ ጋር ከተቃረነ ላለመቀበል እስከመሰዋት ድረስ እንኳን ዝግጁ ነበሩ። | ፊሊጶስ ***በሐዋ.ስራ 6: 5*** ላይ ቤ/ክ ስራ ከተመረጡት ሰባቱ ሰዎች ውስጥ አንዱ ነበረ።ቆየት ብሎም ወንጌላዊ በመሆን ወንጌልን ወደ ሰማሪያ አመጣ።በሰማሪያ የወጌልን እሳት በማስነሳት መሀል ላይ ቢሆንም እንኳን ጌታ ለአንድ ከኢትዮጵያ ለመጣ ሰው ለውጥና ጥምቀት ፊሊጶስን ሊጠቀመው ስለፈለገ ወደ ጋዛ በረሀ ሀገር ላከው።ይህ እንደተፈፀመ ፊሊጶስ በተአምር ተነጠቀ እና በሌሎች ቦታዎች ወንጌል መስበኩን ቀጠለ። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. የእስጢፋኖስ ባህሪ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ ፣ጥሩና እውነተኛ የሆነ ህይወት እንዳለው (***ሐዋ.ስራ 6: 3)***፣በእምነት፣በሀይል***(ሐዋ.ስራ 6: 8)*** እና በጥበብ***(ሐዋ.ስራ 6: 10)*** እንደተሞላ እና ለጌታ ስራ ንቁ እንደሆነ***(ሐዋ.ስራ 6: 8)*** ክርስቲያን ነው የሚገለፀው።<br>2. በሀሰት በአይሁድ መሪዎች ሲታሰር እስጢፋኖስ ራሱን የተከላከለው የአይሁድ ህዝብ ጌታ ኢየሱስን ያለማቋረጥ መቃወማቸው ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ትልቁ ወንጀላቸው “ፃድቅ የሆነውን”መግደላቸው እንደሆነ የከሰሱትን ሰዎች በማስታወስ ነው።***(ሐዋ.ስራ 7: 52)***<br>3. እስከ ሞት ድረስ በወገሩት በጣም በተናደዱ ሰዎች ቢከበብም እንኳን እስጢፋኖስ ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሱን ለጌታ አደራ ሰጠ። ***(ሐዋ.ስራ 7: 59)*** እና ለገዳዮቹ ፀለየና “አንቀላፋ”።***(ሐዋ.ስራ 7: 60)*** እዚህ ጋር “እንቅልፍ” የሚለው ቃል ጌታ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመውሰድ እስኪመለስ ድረስ ሰውነቱ “የሚያንቀላፋው”ን ይገልፃል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል – እስጢፋኖስ ተሰዋ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ፊሊጶስ ሄዶ ለኢትዮጲያዊው ለመስበክ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ታዛዥ ነበር።<br>2. ኢትዮጲያዊው ከአፍሪካ ወደ እየሩሳሌም የመጣው ለማምለክ ነበር ነገር ግን ስለ ወንጌሉ ያለምንም እውነተኛ መረዳት ተመለሰ።እርዳታ ለማግኘት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለከተ።<br>3. ፊሊጶስ በጌታ በመመራት በትክክለኛው ሰዓት ላይ ደረሰ እና ***ኢሳያስ 53ን*** አብራራለት።ምእራፉ ሙሉ በሙሉ እንዴት ስለ ጌታ ኢየሱስ ህይወትና ሞት እንደሚያወራ አሳየው።<br>4. ኢትዮጲያዊው በጌታ ኢየሱስ አመነ በፍጥነትም በውኃ ተጠመቀ በደስታ ወደ ቤቱ ተመለሰ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – ፊሊጶስና ኢትዮጲያዊው ጃንደረባ** |
| **እዲታወስ** | ተማሪዎች ቁልፍ ጥቅሱን ማወቃቸውን አረጋግጡና እንዴት ትምህርቱን እንደሚያጠቃልል ደግሞ ጌታ ኢየሱስና እስጢፋኖስ ለገዳዮቻቸው በመፀለያቸውና መንፈሳቸውን ለእግዚአብሔር በማስረከባቸው ***(ሉቃስ 23: 34 እና ሐዋ.ስራ 7: 60)*** ከሁለቱም ጋር እንዴት እንደሚገናኝ አብራሩ። ***(ሉቃስ 23: 46 እና ሐዋ.ስራ 7: 60)*** | ይህን ጥናት ***ከኢሳያስ 53*** ጋር አገናኙ።ይህ ምእራፍ እንዴት ከ740-680 ከክርስቶስ ልደት በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተፃፈ እና የኢሳያስ ትንቢት በትክክል የጌታ ኢየሱስን ሞት፣መቀበር፣ትንሳኤና እርገቱን እንደሚናገር ግለፁ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ለጌታ ኢየሱስ ታማኝ በምንሆንባቸው ጊዜያት?<br>2. የእስጢፋኖስ ለጌታ መሰጠት በመንግስት የወጡ አንዳንድ ህጎች ከቅዱስ ቃሉ ጋር የተቃረኑ በሚሆኑበት ጊዜ ለእርሱ ለመሰጠት እኛን እንዴት ነው የሚያነሳሳን? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ጌታ ለእርሱ ስራ እንድንሰራለት በሚጠራን ጊዜ ያለምንም ጥያቄ እንታዘዘዋለን?<br>2. እንደ ክርስቲያን ለጌታ ኢየሱስ ጥሩ ምስክሮች ለመሆን በመጣር ሌሎች ወደ እርሱ ሲመጡ በማየት ለተሰጠን ሀላፊነት እንዴት ነው እየኖርን ያለነው? |

| | **ለ5 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 3 – የጌታ ሰራተኞች**<br>**ርእስ – ለመስማት የተዘጋጀ!** | **ለ5 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 3 – የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች**<br>**ርእስ – ቆርኔሌዎስ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሐዋ.ስራ 8: 5፤ 26-40***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሐዋ.ስራ 16: 31***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. የፊሊጶስ በፍጥነትና እና ያለምንም ጥያቄ መታዘዙ ጌታ ኢትዮጲያዊውን ወደ እርሱ ለማምጣት እንዲጠቀመው ምክንያት ሆኗል።<br>2. ኢትዮጲያዊው ለጌታ በመታዘዙ ምክንያት መንገዱን በሀሴት ተሞልቶ ሄደ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሐዋ.ስራ 10: 1-8፤ 23-48***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሐዋ.ስራ 10: 43***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ወንጌል ለሁሉም ነው፣አይሁድና አህዛብ እኩል ናቸው።<br>2. ቆርኔሊዎስ እና ቤተሰዎቹ ከመጀመሪያዎቹ በጌታ ኢየሱስ ካመኑ አህዛቦች መሀል ናቸው። |
| **አስተዋውቁ** | አንዳንዴ እግዚአብሔር እኛ ልንሰራ ካሰብነው በጣም የተለየ ነገር እንድንሰራ እንደሚፈልግ አብራሩ።<br>ፊሊጶስ በሰማሪያ ለጌታ ትልቅ ስራ እየተሰራ እያዩ እንደነበር አብራሩ።ቢሆንም ግን ብዙዎች እየተለወጡ ያለበትን ቦታ ትቶ ለአንድ ኢትዮጲያዊ ለሆነ ሰው ብቻ መንፈሳዊ እርዳታን ለመስጠት በረሀ ወደሆነ ጋዛ ወደሚባል ቦታ ጌታ ላከው። | በአይሁድና በአህዛብ መካከል ያለውን ነገር እና እንዴት አይሁድ የሆነ ሰው በጣም ትንሽ ግንኙነት ሊኖረው እንደሚችል በተጨማሪም ወደ አህዛብ ቤት መሄድ እንደማይችል በቀላሉ አብራሩ።<br>ቆርኔሊዎስ ሮማዊ ባለስልጣን (አህዛብ) ፣የመቶ አለቃ፣በቂሳርያ ከተማ ውስጥ የሚኖርና በውትድርናም ስመጥር የነበረ ሰው ነው። መልካም ህይወት እየኖረ ቢሆንም እንኳን ጌታ ኢየሱስን አያውቅም ነበር።<br>ቢሆንም ግን ለኃጢአቱ ይቅርታን ለማግኘት በቅንነት ይፈልግ ነበር እናም እግዚአብሔርም ይህን በማየቱ ወንጌልን ከሰበከለት ከጴጥሮስ ጋር እርሱ እና ቤተሰቡ ተገናኙ። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ፊሊጶስ ኢትዮጲያዊውን ሲያገኘው ***ኢሳያስ 53: 7-8ን*** እያነበበ ነበር እና ፊሊጶስ ይህን አጋጣሚ ስለ ጌታ ኢየሱስ ሞትና ህይወት ለማውራት ተጠቀመው።<br>2. ኢትዮጲያዊው ኢሳያስ የፃፈው አዳኙ ለመሆን በመስቀል ላይ ስለ ሞተው ጌታ ኢየሱስ መሆኑን ከፊሊጶስ ተማረ እና ኢትዮጲያዊው ኃጢአተኛ መሆኑን አስተዋለና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን እንደ አዳኙ ተቀበለ።<br>3. ፊሊጶስ ለኢትዮጲያዊው ለመጠመቅ ያለውን መብት አስረዳውና ወደ ውኃ ሲደርሱ ፊሊጶስ አጠመቀው። ከኢትዮጲያዊው ጋር ሲጓዙ የነበሩ ሰራተኞች ጥምቀቱን መመስከር ብቻ ሳይሆን በዚያ ጊዜ የናዝሬቱ ኢየሱስ ተብሎ የሚጠራውን ተከታይ በመሆኑ ኢትዮጲያዊው አሁን ምን ያህል ደስተኛ እንደሆነ አይተው ይሆናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – ፊሊጶስና ኢትዮጲያዊው ጃንደረባ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን *ታሪክ* አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ቆርኔሌዎስ አንድ ቀን ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት አካባቢ አንድ የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲመጣ በራእይ በግልጥ አየው እናም ወደ ኢዮጴ ለጴጥሮስ ሰዎችን እንዲልክ አዘዘው።<br>2. ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሲመጣ እርሱ ሲሰብክ ለመስማት የተገኙ ሌሎች ሰዎችም ነበሩ።<br>3. ጴጥሮስ እግዚአብሔር ሰውን ከሰው እንደማይለይ መዳን ለአይሁድና ለአህዛብም ጭምር እንደሆነ ለተሰበሰቡት ተናገረ።<br>4. ጴጥሮስ ለተገኙት ሰዎች ስለ ጌታ ኢየሱስ ህይወት፣ሞትና ትንሳኤ ሰበከና በእርሱ ካመኑ ለኃጢአታቸው ይቅርታን እንደሚያገኙ በመናገር ጨረሰ።<br>5. የተገኙት አህዛቦችም ይህንን ነው ያደረጉት በጌታ ኢየሱስ ካመኑና ከተጠመቁ ከመጀመሪያዎቹ አህዛቦች ውስጥ ሆኑ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ስለኢየሱስ ነገረው** |
| **እዲታወስ** | ይህን ትምህርት ***ከኢሳያስ 53*** ጋር አያይዙና ***ቁጥር 7 እና 8ን*** ደግሞ ለይታችሁ አብራሩ።በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ ጌታ ኢየሱስን መስቀሉን ተቋቋመ።ትክክለኛ ፍርድ አልተፈረደለትምና በህይወቱ መጀመሪያዎች ላይ ነበር የተቀጨው፤ስለ ኃጢአታችንም ተሰቀለ። | እንደ አይሁድ ወደ አህዛብ ቤት ሲገባ የጴጥሮስን ቦታ አስቡ።ጴጥሮስ ምን ማድረግ እንዳለበትና ወንጌልን ለአህዛብ ስለማምጣት እንዴት ማሰብ እንዳለበት እንዴት ምሪት እንደተሰጠው ለማየት ***ሐዋ.ስራ 10: 9-17ን*** ተመልከቱ። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ታዛዥ የሆኑ ክርስቲያኖች እውነተኛ በረከትን ወደ ሌሎች ህይወት እንደሚያመጡ ፡ ክርስቲያን ለሆኑም ላልሆኑም ሰዎች።<br>2. በጌታ በኢየሱስ የሆነ የግል እምነትን ጥምቀት መከተል አለበት። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. የኃጢአትን ይቅርታ ዘር፣ባህል ወይንም ሀይማኖት ሳይገደበው ሁሉም ሰው ማግኘት እንደሚችል ለመረዳት?<br>2. በህይወታችን ምን ማድረግ እንዳለብንና ኃጢአታችን እንዴት ይቅር እንደሚባል ለማወቅ አሁን የሚመራን መጽሐፍ ቅዱስ ስላለን ለዚህ ራእይ እንደማያስፈልግ ለመረዳት? |

| | **ለ5 – ደረጃ 3**<br>**ትምህርት 4 – የጌታ ሰራተኞች**<br>**ርእስ – ለመሄድ ተዘጋጅ!** | **ለ5 – ደረጃ 4**<br>**ጥናት 4 – የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች**<br>**ርእስ –በርናባስ** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሐዋ.ስራ 10: 1-20፤ 24-29፣ 33-43***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሐዋ.ስራ 10: 43***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ቆርኔሌዎስ በጣም ጥሩ ሰው ቢሆንም እንኳን እንዴት ክርስቲያን መሆን እንዳለበት የሚነግረው ሰው ግን ይፈልግ ነበር።<br>2. ጴጥሮስ በራእዩ ምክንያት ወንጌል ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም እንደሆነ ተማረ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ሐዋ.ስራ 4: 32-37፣ 9: 26-31፤ 11: 19-30***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሐዋ.ስራ 11: 24***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ጥሩ ነገርን በመስራት ክርስቲያን ልንሆን አንችልም።<br>2. ክርስቲያኖች መልካም የሚያደርጉት "መልካምነት" በክርስቲያን ህይወት ውስጥ አንዱ የመንፈስ ፍሬ ስለሆነ ነው። ***(ገላቲያ 5: 22)*** |
| **አስተዋውቁ** | ይህ ታሪክ የተካሄደው በባህር ዳር በሚገኝ በቂሳርያ ከተማ ነው ።ቆርኔሌዎስ በዚህ ከተማ በውትድርና ውስጥ ያለ ሮማዊ ባለስልጣን ነበር እናም እንደ መቶ አለቃ የመቶ ሰዎች ሀላፊ ነበር።በዚያ ካሉት ከአንዱ የጣሊያን የጦር ሰራዊት ጋር የተያያዘ ነበር።ምንም ቢሆን ግን እግዚአብሔርን የሚፈልግ አህዛብ ሰው ነበር። ነገር ግን እስከዚህ ጊዜ ድረስ ጴጥሮስ ወንጌልን ይናገር የነበረው መሰሉ ለሆኑ አይሁዶች ብቻ ነው። | ***በሐዋ.ስራ 4: 36*** ላይ መጀመሪያ በርናባስን እናያለን።የስሙ ትርጉምም "የመጽናናት ልጅ" ማለት ነው።ከቆጵሮስ ደሴት ነበር የመጣው እና መሬቱን ሸጦ ብሩን አምጥቶ ለሀዋርያቱ እንደሰጠ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።የእርሱ ደግነት ለሐዋርያቱ ትልቅ መጽናናት ይሆናቸው ዘንድ እንደ ስሙ ለመሆን እየኖረ ነበር። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. መልአኩ በራእይ ለቆርኔሌዎስ በቂሳርያ በደቡብ በኩል ኢዮጴ ወደሚባል ከተማ ጴጥሮስ ለተባለው ስምኦን ሰዎችን እንዲልክ ይነግረዋል።<br>2. ከአንድ ቀን በኋላ ጴጥሮስ ሊፀልይ በወጣበት ጣራው ላይ ሳለ ራእይ አየ።እግዚአብሔር ለጴጥሮስ ወንጌል ለአይሁድ ብቻ የተገደበ እንዳልሆነና ለአህዛብም ጭምር መሆኑን ገለጠለት።እግዚአብሔር ሰዎችን በሁለት ክፍል ብቻ ነው ለይቶ የሚያየው ፡ የእርሱ የሆኑትና ያልሆኑት!<br>3. ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሲደርስ የእግዚአብሔር በረከት ለእስራኤላውያን አይሁዶች ብቻ የተገደበ መሆኑን ያምን እንደነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰው እደማያደላ መማሩን ተናገረ።***(ሐዋ.ስራ 10: 34)***<br>4. ጴጥሮስ ለተገኙ ሰዎች ወንጌልን ሰበከና መዳን "ለሚያምን ሁሉ" እንደሆነ አጥብቆ ተናገረ። ***(ሐዋ.ስራ 10: 43)*** የተገኙት ሰዎች አመኑ እናም ተጠመቁ።ይህ የአህዛብን ወደ ቤተክስቲያን መግባት መጀመሪያ ያሳያል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ:ስዕል – ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ስለ ኢየሱስ ነገረው።** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. በርናባስ ራስ ወዳድ ባለመሆኑ የተሰጠ የጌታ ሰራተኛ ነበር።ጊዜውንና ንብረቱን ሌሎች ለመርዳት ነበር የሚጠቀመው።ሰዎች እግዚአብሔርን ወደማወቅ ሲመጡ ማየትና የህይወት መሰረታዊ ፍላጎቶችን በማጣት የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት ይፈልግ ነበር።በውጤቱም "ደግ ሰው" ተባለ። ***(ሐዋ.ስራ 11: 24)***<br>2. በርናባስ ለጳውሎስ ደግነትን አሳየ። ***(ሐዋ.ስራ 9: 27)*** በእየሩሳሌም የነበሩ ክርስቲያኖች ጳውሎስን ለመቀበል በፈሩ ጊዜ በርናባስ ሀላፊነትን ወሰደ።<br>3. በርናባስ በአንጾኪያ የተመሰረተውን አዲስ ቤተ ክርስቲያን እንዲያበረታታ በእየሩሳሌም በነበረው ቤ/ክ ተልኮ ነበር እናም በዚያ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ ተመለሱ።በአንጾኪያ የነበሩትን አዲስ ክርስቲያኖች "በጌታ ፀንተው ይኖሩ ዘንድ" መከራቸው። ***(ሐዋ.ስራ 11: 23)*** ምንአልባትም ለአዲሶቹ ክርስቲያኖች ከዚህ የበለጠ ጥበበኛ ቃል ተነግሯቸው አያውቅ ይሆናል!<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: የሚሆን ስዕል የለም** |
| **እዲታወስ** | ቁልፍ ጥቅሱን አጥኑና የዛሬውን ትምህርት እንዴት እንደሚያጠቃልል አብራሩ። በተጨማሪም ***በዮሐንስ 3: 15-16*** "የሚያምን ሁሉ" ወደሚለው ሀረግ ተማሪዎች አመልክቱ። | በጥናት አራት ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በትክክል እንዲመልሱ ለመርዳት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይህንን ጥናት ከልሱ። |
| ***የተግባር ሥራ*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ለሁሉም ሰዎች ወንጌልን ለማካፈል?<br>2. በራሳችሁ ቃል ***ሐዋ.ስራ 10: 34ን*** አብራሩ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. እንደ ክርስቲያን "መልካምነትን" በህይወታችን ለማሳየት?<br>2. እንደ ክርስቲያን ለጌታ እውነተኛ ለመሆን? |

| | ለ6 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የዮሴፍ ህይወት<br>ርእስ – ወጣቱ ህልመኛ | ለ6 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – ያእቆብ እና ቤተሰቡ<br>ርእስ – በካራን |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዘፍጥረት 37: 1-11***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 37: 8***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ዮሴፍ ገና የአስራ ሰባት አመት ልጅ እያለ እግዚአብሔር በህልም አናገረውና ለህይወቱ እቅድ እንዳለው ገለጠለት።<br>2. የቅንአት ኃጢአት እግዚአብሔርን አያከብረውም ደግሞ ወደ ከባድ ኃጢአትም ሊያድግ ይችላል ስለዚህ ሊወገድ ይገባል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዘፍጥረት 29: 1-30***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ገላቲያ 6: 7***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራል የእርሱ ጊዜም ደግሞ ትክክል ነው።<br>2. በህይወታችን ውስጥ ኃጢአትን የምንዘራ ከሆነ ፍሬውንም እንደምናጭድ ማሰብ ይኖርብናል። |
| አስተዋውቁ | የዮሴፍን አባቶች አብርሃምን፣ይስሐቅን እና አሁን ያእቆብና ቤተሰቦቹን ለተማሪዎች አስታውሱ።ዮሴፍ ከያእቆብ ልጆች መሀል አንዱ ነበር እናቱ ራሄል ነበረች።ስራው እረኝነት ነበር። ቢኒያም የሚባል ታናሽ ወንድም ነበረው ቢኒያምን ስትወልድ ነበር የዮሴፍ እናት ራሄል የሞተችው። | የያእቆብን አባቶች ለተማሪዎች አስታውሱ።ያእቆብ የይስሀቅና የርብቃ ልጅ ሲሆን ኤሳው ደግሞ ወንድሙ ነበር።<br>በቤርሳቤህ ይኖር ነበር እና ያእቆብ ብኩርናውን ስለወሰደበት ኤሳው ሊገድለው በማሰቡ በሜሶፖታሚያ ወደሚገኘው ካራን ሸሸ።<br>(ታሪኩን በአጭሩ አጠቃሉ)<br>ያእቆብ ከቤርሳቤህ ወጥቶ ሲሄድ 77 አመቱ ነበር፤አጎቱን ላባን በማገልገል 20 አመት ፣33 አመት በከንአን እና የመጨረሻዎቹን ሰባት አመታት በግብጽ አሳለፈ።<br>ከቤርሳቤህ እስከ ካራን ለመጓዝ 800ኪ.ሜ ያህል ነው። |
| አጠናቁ | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br><br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br><br>1. የሰሩትን ትክክል ያልሆነ ነገር ለያእቆብ በመናገሩ ምክንያት ዮሴፍ በወንድሞቹ ተጠልቶ ነበር እናም ደግሞ የራሄል ልጅ በመሆኑና በእርጅና ያገኘው ልጅ ስለሆነ ያእቆብ ይወደዋል።<br>2. ባለ ብዙ ቀለሞች የሆነው ኮት የተዋበ፣ረዥምና እጅጌ ሙሉ ካባ በመስጠቱ ያእቆብ ለዮሴፍ ያለውን ልዩ ፍቅር ያሳያል ነገር ግን በወንድሞቹ ልብ ቅንአትን፣ ጥላቻንና ክፋትን አነሳሳ።<br>3. በዮሴፍ በመጀመሪያው አስራ አንዱ ነዶዎች ለአስራ ሁለተኛው ነዶ ሲሰግዱ ያለመው ህልም አንድ ቀን ወንድሞቹ እንደሚሰግዱለት የሚያሳይ ትንቢት ነበር።ሁለተኛውም ህልም ወንድሞቹ፣ ራሄል ስለሞተች ከያእቆብ እና (ፀሀይ) ከሊያ(የእንጀራ እናቱ)(ጨረቃ) ጋር ለእሱ እንደሚሰግዱለት የሚያሳይ ትንቢት ነበር።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ህልመኛው ዮሴፍ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br><br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. እግዚአብሔር ከሀራን የመጡት እረኞች ከብቶታቸውን እያሰማሩ ወዳለበት እና ራሄል ከብቶችን ውሀ ልታጠጣ ወደ መጣችበት ሜዳ ያእቆብን የመራበት ሰአት ትክክል ነበር።<br>2. ያእቆብ ራሄልን ማግባት ነበር የፈለገው ነገር ግን ላባ አታለለውና መጀመሪያ ታላቅ እህቷን ሊያን እንዲያገባ አደረገው።ራሄልን ከማግባቱ በፊት ለተጨማሪ ሰባት አመታት ላባን ማገልገል ነበረበት።ቀጥሎም ደግሞ ለሰባት አመታት ማገልገል ነበረበት።<br>3. ያእቆብ ማታለልን ዘርቷል አሁን ደግሞ እያጨደው ነበር!<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ያእቆብ በሰርጉ እለት ተታለለ** |
| እዲታወስ | በትምህርት አንድ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ለመመለስ እንዲረዳቸው በፈተና መልክ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይህንን ትምህርት ከልሱ። | ተማሪዎች ያእቆብ ከቤርሳቤህ (በምእራብ በወንዝ ዳርቻ) ወደ ካራን (በኤፍራጦስ ወንዝ ላይ) በዛሬው ሲሪያ ያደረገውን ጉዞ በአይምሮአቸው እንዲስሉ እንዲረዳቸው ካርታ ተጠቀሙ። በመካከለኛው ምስራቅ እንደ ሲሪያ፣ዮርዳኖስ እና ኢራቅ ባሉት ሀገሮች ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሀይል በህይወታቸው ከመፈለግ ይልቅ የራሳቸውን ፈቃድ ሀይል ለማሳካት በመጣራቸው ምክንያት እየቀጠለ ወዳለው አለመስማማት ትኩረታቸውን መሳብ ትችላላችሁ። ኃጢአተኞች ሆነን በመወለዳችን ምክንያት ብቻ! የያእቆብ የግል ፈቃድ አሁንም በሰዎች ህይወት ላይ ይሰራል። |
| የተግባር ሥራ | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ህይወት እቅድ አለው።ጌታን እንደ አዳኛችን ስናምነው፣በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን ነገሮች በተግባር ስናደርግና እርሱን በምናስከብርበት መንገድ እንዲመራን እለት እለት ስንፀልይ እቅዱን በህይወታችን ይፈጽማል።<br>2. የቅንአት ኃጢአት ከህይወታችን ልናርቀው የሚገባ ነገር ነው፤መጽሐፍ ቅዱስ “እንደ ሲኦል የጨከነ” ብሎ ይገልፀዋል። ***(መሀልየ መሀልይ ዘሰሎሞን 8: 6)*** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ለኃጢአታችን ንስሀ ካልገባንና ለመዳን አዳኛችንን ካላመንን የኃጢአተኛ ህይወታችንን ውጤት እንደምናጭድ የማወቃችን ጥቅም።<br>2. እኛ ክርስቲያኖች ከሆንን እና ኃጢአት ከሰራን በፍጥነት ለጌታ ኢየሱስ ተናዘን ይቅርታውን መቀበል(***1 ዮሐንስ 1: 9)***፤ በተጨማሪም በህይወታችን ጭንቀት ብቻ ሚያተርፉልንን አጋጣሚዎች ከማምጣቱ በፊት ከእርሱ መሸሻችንን የማረጋገጥ ጥቅም። |

| | ለ6 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – የዮሴፍ ህይወት<br>ርእስ – የተጠላው ወንድም | ለ6 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – ያእቆብ እና ቤተሰቡ<br>ርእስ – በጽኒኤል |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዘፍጥረት 37: 12-36***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ሮሜ 6: 12***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ኃጢአት በህይወታችን በትንሹ ሆኖ ነው የሚጀምረው እናም ጌታ ኢየሱስን ይቅርታ ካልጠየቅነው በስተቀር ያድግና ህይወታችንን ይቆጣጠረዋል።<br>2. ስለ ኃጢአታችን ጥፋተኝነት ሲሰማን ለጌታ ኢየሱስ መናዘዛችን በጣም አስፈላጊ ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡** ***ዘፍጥረት 32: 1-32***<br>**ቁልፍ ጥቅስ፡** ***ዘፍጥረት 32: 11***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ያእቆብ መለኮታዊ ጥበቃ በመፈለግ ስሜት ተነስቶ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ።<br>2. ያእቆብ በመጨረሻም ህይወቱን ለእግዚአብሔር ሰጠ ከዚያም ስሙ ያእቆብ ማለትም "አታላይ" እንደነበረ ተናገረ ። እግዚአብሔር ስሙን ወደ እስራኤል ቀየረው ማለትም "ልዑል እግዚአብሔር"። |
| **አስተዋውቁ** | እስካሁን ያለውን የዮሴፍን ታሪክ ከልሱና በያእቆብ ቤተሰብ ውስጥ የነበረውን ጭንቀትና ምክንያቱን ለተማሪዎች አስታውሱ።<br>***በዘፍጥረት 27*** ላይ ያእቆብ አባቱን ይስሀቅን ከኤሳው በፊት እንዲባርከው የፍየል ቆዳ በመጠቀም አታለለው።በዚህ ትምህረት የያእቆብ ልጆች በፍየል ደም ተጠምቀው አታለሉት።ልጆቹ ሲያታልሉት ያእቆብ ይህንን ሊያስታውስ እንደሚችል ማሰብ ምክንያታዊ ነው። የማታለል ህመም በድጋሜ በያእቆብ ህይወት ተሰማው! | ተማሪዎች ከተፈላጊ ሰዎች ጋር ስለተገናኙበት ማንኛውም አይነት አጋጣሚ አብራሩ ።በዚህ ጥናት ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት እያሰብን እንዳለ እና ይህ በያእቆብ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ አስረዱ።ከያእቆብ ጋር የታገለው ሰው ***(ቁጥር 24)*** ማንም ሳይሆን ጌታ እራሱ ነው።***ሆሴዕ 12: 4*** አንብቡ።በተጨማሪም ጌታ (ሀ) ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ለሙሴ እንደተገለጠለት ***(ዘፀአት 3: 1-22)*** (ለ) በትሩን ወደ እባብ በተለወጠበትና እጁ በለምጽ በተሸፈነበትን ሁለት አጋጣሚዎች ለሙሴ እንደተገለጠለት ***(ዘፀአት 4: 1-17)*** (ሐ) ለኢሳያስ ከጥያቄ ጋር እንደተገለጠለትና የኢሳያስ ምላሽ **(ኢሳያስ *6)*፤** (መ) ለሳውል በደማስቆ ላይ መንገድ እንደተገለጠለት ***(ሐዋ.ስራ 9: 1-19)*** ተመልከቱ።እነዚህ ሁሉም ሰዎች ከጌታ ጋር በጣም አስፈላጊ ግንኙነት እንደነበራቸው እና በውጤቱም በጣም የሚታወሱ ገጠመኞችን እንዳገኙ አጉልታችሁ ተናገሩ። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ወንድሞቹ ለዮሴፍ የነበራቸው ጥላቻ ወደ ጉድጓድ እስኪወረውሩት ድረስ የሚያደርስ ነበር።<br>2. የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብጽ እየተጓዙ ለነበሩ እስማኤላውያን (ምድያማውያንም ተብለው ይጠራሉ) በሀያ የብር ሸጡት።<br>3. የዮሴፍ አባት ያእቆብ ወንድሞቹ ውሸት የሆነ ነገር ስለነገሩት ልቡ ተሰብሯል።በፍየል ደም ውስጥ የተነከረ ኮት አሳዩት እናም ያእቆብ ልጁ እንደሞተ አሰበ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – ዮሴፍ እንደ ባሪያ ሲሸጥ።** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ያእቆብ ከካራን ወደ ከነዓን በመመለስ ላይ ሳለ ኤሳው ከሀያ አመታት በፊት እንደተናገረው ይገለኛል ብሎ ስላሰበም ፈራ። ***(ዘፍጥረት 27: 41)***<br>2. ያእቆብ ኤሳው ከ400 ሰዎች ጋር እየመጣ እንደሆነ ሰማ ስለዚህም የመጀመርያው ክፍል ከተጎዳ ሁለተኛው ክፍል እንዲሸሽ በማሰብ ቤተሰቡን በሁለት ክፍል ከፈለ።<br>3. ያእቆብ ኤሳውን ለመለማመጥ በተከታታይ ሶስት መንጋ፣ ባጠቃላይ 580 እንስሳትን ላከ።<br>4. ያእቆብ ምሽቱን በጵኒኤል (የእግዚአብሔር ፊት) ብቻውን አሳለፈ-የህይወቱ ትልቁ ገጠመኝ።ጌታም የያእቆብን የጭኑን ሹልዳ ነካው፣ጭኑንም ከመጋጠሚያው ላይ አናጋውእና ስሙን ከያእቆብ ወደ እስራኤል ለወጠው።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል ያእቆብ ወደ ከነአን ተመለሰ።** |
| **እዲታወስ** | በዚህ ታሪክ ውስጥ ዮሴፍን የፈርኦን አንዱ ሀላፊ ለነበረው ለጴጢፋራ ለመሸጥ ወደ ግብጽ ነፃ ጉዞ እንዳዘጋጁለት እስማኤላውያኖቹ ባያውቁም እንኳን እግዚአብሔር ግን እንዴት እየተቆጣጠረ እንደነበር አብራሩ።<br>እግዚአብሔር ዮሴፍን በብዙ የሚባርከው በግብጽ ነበር እናም ዮሴፍ በግብጽ ምድር ለይ ሁሉ በስልጣን ሁለተኛ ይሆናል።<br>***በመዝሙር 76: 10*** እግዚአብሔር የሰውን ቁጣ ለክብሩ ማድረግ እንደሚችል እና የማያከብረውንም እንደሚገታ ማሳየቱን አስረዱ። | ተማሪዎች በጥናት ሁለት የተጠየቁትን ጥያቄዎች ለመሙላት የሚረዳቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይህን ጥናት ከልሱ።<br>ትኩረታቸውን ቀጥሎ ባሉት ቃላት ትርጓሜ ላይ አድርጉ፡<br>መሀናይም ***(ቁጥር 2***) - ሁለት ተቀባይ ወይንም ሁለት ሰፈር።<br>ያእቆብ ***(ቁጥር 27)*** - የሚተካ ወይንም "አታላይ"።<br>እስራኤል ***(ቁጥር 28)*** - ከእግዚአብሔር ጋር የሚታገል ወይንም የእግዚአብሔር ልዑል።<br>ጵኒኤል ***(ቁጥር 30)*** - የእግዚአብሔር ፊት። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ተማሪዎች ለሆነ ሰው በልባቸው ጥላቻ ወይንም ቅናት ተሰምቷቸው የሚያውቅ እንደሆነ አወያዩ? ከሆነ ሁሉም ኃጢአታቸውን ለጌታ ኢየሱስ መናዘዝና ከሁለቱም ክፋቶች ነፃ ሆነው የሚኖሩበትን ሀይል እንዲሰጣቸው መጠየቅ አለባቸው።<br>2. ቁልፍ ጥቅሱን ***ሮሜ 6: 12ን*** ተማሩና ተማሪዎች ህይወታቸውን የሚመሩበት መርህ እንዲያደርጉት አበረታቱ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ያእቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻውን ቀርቶ ነበር። (ቁጥር 24) እንደ ኃጢአተኛ ለመዳን በግል ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ሊኖረን ይገባል።ሁሉም ሰው ኃጢአቱ ይቅር እንዲባልለት ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት አለበት!<br>2. መልአኩ ከያእቆብ *ጋር ታገለ (ቁጥር 24)* እና ከራስ ክብር እና ከግብዝነቱ ነፃ አወጣው።ለሁላችንም ይህን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።<br>3. ያእቆብ ስሙ ተቀየረለት።ሁላችንም ስማችን ወደ ክርስቲያን ሊለወጥ ይገባል፤ ከዚያም የተቀየረ አመለካከት፣በእግዚአብሔር ፊት የተቀየረ አቋም፣ከእግዚአብሔር ጋር የተቀየረ ግንኙነት እና በእግዚአብሔር ፊት የተቀየረ አረማመድ። |

| | ለ6 – ደረጃ 3<br>**ትምህርት 3 – የዮሴፍ ህይወት**<br>**ርእስ – ታማኙ እስረኛ** | ለ6 – ደረጃ 4<br>**ጥናት 3 – ያእቆብ እና ቤተሰቡ**<br>**ርእስ – በቤቴል** |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ዘፍጥረት 39: 1-6፣ 19-23***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 39: 21***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. ዮሴፍ ከቤቱ ርቆ በግብጽ ቢሆንም እንኳን በጣም ከባድ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥም ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ቆይቷል።<br>2. እግዚአብሔር አይኑን በዮሴፍ ላይ አድርጎ ነበር ወደፊትም ለእርሱ ያስቀመጠው ትልቅ ነገር ነበረው። ***(ሮሜ 8: 28)*** | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ዘፍጥረት 35: 1-15***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***መዝሙር 37: 7***<br><br>**የምንማረው፡**<br>1. እንደ ክርስቲያን እግዚአብሔር ለህይወታችን ካለው መንገድ ተቅበዝብዘን ልንጠፋ እንችላለን ነገር ግን እርሱ ፈጽሞ አይተወንም ከቶም አይጥለንም።<br>2. እንደ ክርስቲያን ላለፈው የህይወት ውድቀታችን እና ወደፊት ሊገጥሙን ስለሚችሉ ከባድ ሁኔታዎች እና ፈተናዎች እርዳታ ያስፈልገናል። |
| **አስተዋውቁ** | ንፁህ ሆነው ሳለ ሰዎችን እስር ቤት ስለሚያስገባ ኢፍትሀዊ ነገር አብራሩ።ይህ ዮሴፍ ለይ እንደደረሰ አስረዱ።<br>አማኞች ዛሬ በአንዳንድ ሀገሮች በእስር ቤት ውስጥ ናቸው።እስር ቤት ያሉት ምንም ስህተት ፈጽመው ሳይሆን ልክ እንደ ክርስቲያን መሆን እንደለባቸው ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆን ዝግጁ በመሆናቸው፣በማመንና ከመጽሐፍ ቅዱስ የተማሩትን በመታዘዛቸው ምክንያት ነው። | ትኩረታቸውን በጌታ የሚያምኑ አስተማማኝ ጥበቃ እንዳላቸው በመሳብ ጥናቱን አስተዋውቁ ፤ በጌታ ውስጥ ደህንነት አለ። ***መዝሙር 91*** እና ***ሮሜ 8*** ይህን ጥበቃ ያሳያሉ።ከጥሎ ያሉት ጥቅሶች ልትመለከቷቸው ይገባል ለማስተዋወቅና እንደ መነሻ ሀሳብ እንዲሆኑ፡ ***መዝሙር 91: 2፣ 15*** እና ***ሮሜ 8: 31***። |
| **አጠናቁ** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br><br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ዮሴፍ በፈርኦን ቤተ መንግስት ውስጥ ሀላፊ ለነበረው ለጴጢፋራ እንደ ባርያ በእስማኤላውያን ተሽጦ ነበር።<br>2. የጴጢፋራ ሚስት ስለ እርሱ ዋሸች ፣በውሸት ተከሰሰና እስር ቤት ውስጥ ተጣለ።<br>3. ዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ በጣም ጥሩ ባህሪይ ከማሳየቱ የተነሳ የእስር ቤት አዛዡና ሀላፊ ሆነ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል – ዮሴፍ እና የጴጢፋራ ሚስት።** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br><br>**ማብራራታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ያእቆብ ***በዘፍጥረት 28: 20-22*** ላይ ከሰላሳ አመታት በፊት የገባውን ቃል እንዲፈጽም እግዚአብሔር አዘዘው እናም ወደ ቤቴል ተመለሰ።<br>2. ያእቆብ ሌሎች አማልክትን እንዲያስወግዱና ልብሳቸውን እንዲያጥቡ ቤተሰቡን አዘዘ እናም ይህን ሲያደርጉ ለአረመኔያዊ ጎረቤቶቻቸው ሽብር ሆኑ።<br>3. በ"ኤል ቤቴል" መሰዊያን ሰራ እና ከኤሳው የጠበቀውን እግዚአብሔርን አመለከ።<br>4. እግዚአብሔር በድጋሚ በቤቴል ከያእቆብ ጋር ተገናኘ እና ከአብርሃምና ከይስሀቅ ጋር ያደረገውን ኪዳን አደሰ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ዮሴፍና ኤሳው በድጋሚ ተገናኙ** |
| **እዲታወስ** | እግዚአብሔር ለዮሴፍ ህይወት እንዴት የሰይጣንን ሀሳብ እንደሚመታ እናም ዮሴፍ ስህተት እንደሌለበት፣ታማኝ እና ሀላፊነት የሚሰማው አማኝ ሆኖ እንዴት ወደ ላይ እንደወጣ ተማሪዎች እንዲያስረዱ በመጠየቅ ትምህርቱን ከልሱ። | ራሄል የልጇን ስም ቤንኦኒ ብላዋለች "የመከራዬ ልጅ" ማለት ነው ነገር ግን ያእቆብ ቢኒያም አለው፤ይህም "የቀኜ ልጅ" ማለት ነው።ይህ ጥናት የመስቀል ላይ መከራን ስለሚቀበል እና በእግዚአብሔር ቀኝ በመንግስተ ሰማይ ስለሚቀመጥ እንዴት ሌላ ውልደትን በስም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አስቀድሞ እንዳሳየ አብራሩ። ልክ ቤቴል ለያእቆብ የማይረሳ ቦታ እንሆነ ሁሉ ቀራንዮም ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እና በእርሱ ለሚያምኑት ያማይረሳ ቦታ ነው። |
| **የተግባር ሥራ** | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ይህ ትምህርት ካመነው እና ከታዘዝነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጣም ከባድ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥም እንዴት ሊንከባከበን እንደሚችል ምን እንዳስተማረን አስቡ።<br>2. እንደ ክርስቲያን ከፈተናና ከመከራ ነፃ አይደለንም። በመንገዳችን ሲመጡ እንዴት ነው ምላሽ መስጠት ያለብን?<br>3. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እምነታቸው የታሰሩ ሌሎች ሰዎችን አስቡ። | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብና ጌታ እለት እለት እንዲመራን በመፀለይ የጌታን በረከት በህይወታችን መፈለግ አለብን።<br>2. በህይወታችን ትልቅ "የቤቴል ትዝታ" የሆነውን ነገር አብራሩ።<br>3. እንደ ክርስቲያን በከባድ ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ***ዕብራውያን 13: 5ን*** አጥብቀን መያዛችንን እርግጠኛ መሆን አለብን -"ከቶ አልተውህም፤ በፍፁም አልጥልህም"። |

| | ለ6 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የዮሴፍ ህይወት<br>ርእስ – አዲሱ መሪ | ለ6 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – ያእቆብ እና ቤተሰቡ<br>ርእስ – በከነዓን |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ዘፍጥረት 41: 14-49***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ዘፍጥረት 41: 32***<br>**የምንማረው፡**<br>1. ዮሴፍ ሁለቱን ህልሞች መተርጎም ስለቻለ ክብሩን ለእግዚአብሔር ሰጠ እናም ለትህትናው እግዚአብሔር ሀላፊነትን ሰጠው።<br>2. ዮሴፍ ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበር እናም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት፡ *ዘፍጥረት 37: 1-36***<br>**ቁልፍ ጥቅስ: *ኤፌሶን 4: 31-32***<br>**የምንማረው፡**<br>1. አድልዎ ወደ ቅናት ያመራል ቅናት ደግሞ በጣም ከባድ ወደ ሆነ ኃጢአት ያመራል እና በሰዎች ህይወት ላይ ውጤትን ያመጣል-በሚቀናውም በሚቀናበትም ሰው ላይ።<br>2. ወንድሞቹ ከነኃጢአታቸው ለብዙ አመታት ቢኖሩም እንኳን ዮሴፍ ከአባቱ ሞት በፊት በድንገት ራሱን ለወንድሞቹ ይገልጣል፤ከዚያም ይቅርታ እና መስማማት ይሆናል።***(ዘፍጥረት 50: 20)*** |
| አስተዋውቁ | እስካሁን ያለውን ታሪክ አስታውሱና እግዚአብሔር በዮሴፍ ህይወት አላማውን እየፈፀመ እንደነበረ አስረዱ።<br>ከዮሴፍ ጥሩ ምስክርነት የተነሳ ***(ቁጥር 39)*** በስልጣን ሁለተኛ ሆኖ እንደተሾመ ጥቀሱ።<br>***በቁጥር 42*** ቀለበቱ የሚያሳየው ከባርያ ቦታ ተነስቶ ወደ ንጉስ ልጅ ቦታ እንደተወሰደ ነው፤በተቀዳደደ ልብስ ቦታ በተልባ እግር የተሰራ ልብስ ተሰጠው፤ወደ ስልጣን መውጣቱን የሚያሳይ የወርቅ ሀብል ተሰጠው፤በተጨማሪም አሁን እስረኛ እንዳልሆነና በፈርኦን መንግስት ውስጥ ነፃነቱን እያጣጣመ እንደሆነ የሚያሳይ ሰረገላ ተሰጠው ***ቁጥር 43*** ።<br>በ17 አመቱ ከውርደት ቦታ ከጉድጓድ ውስጥ ወደ ሀሴት ቦታ 30 አመቱ ሲሆን ተወስዷል።ትልቅ ሀላፊነት ያለው ስራ ውስጥ ያለ በጣም ወጣት ሰው ነበር! | የያእቆብን ቤተሰብ እና ያሉበትን ሁኔታ አስተዋውቁ።<br>ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦችን በመመልከት የዚህን ጥናት መነሻ ሀሳብ አዘጋጁ፡<br>***ሀ. መዝሙር 56*** – ለክርስቲያኖች ሰይጣን ሌሎችን በመጠቀም ሊያጠቃቸው ቢሞክርም እንኳን እግዚአብሔር ግን እንደሚጠብቃቸው አብራሩ።<br>***ለ. ማቴዎስ 5: 43-48፤ ኤፌሶን 4: 22-32*** – በእነዚህ በሁለቱም ጥቅሶች ላይ እንደተገለፀው በጣም ከባድ ቢሆንም እንኳን ጌታንና ተከታዮቹን ከማይወዱ ሰዎች ከሚደርስባቸው የመከራና የጭንቀት ጊዜያት እንደ ክርስቶስን የሚመስል ባህርይ እንዲይዙ ተማሪዎችን አበረታቱ። |
| አጠናቁ | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራሪታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ፈርኦን ህልም ያልምና ህልሙን ለመተርጎም ዮሴፍ ከእስር ቤት ይመጣል።<br>2. ዮሴፍ የፈርኦንን ሁለት ህልሞች ተረጎመ- ሰባት የጥጋብና ሰባት የረሀብ አመታት።ፈርኦን ዮሴፍን በስልጣን ሁለተኛ አደረገው እናም ዮሴፍ የበቆሎ እቅዱን ያስተዳድራል።<br>3. በፍሬያማ አመታት የበቆሎ ክምችት በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ልኬቱን ጽፎ ለማስቀመጥ ይከብድ ነበር።ሰባቱ የረሀብ አመታት ሲመጡ በግብጽና ከዚያም ውጪ ላሉ ለተራቡ ሰዎች ተጨማሪ በቆሎ ነበረ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ዮሴፍ፤እንጀራ ጋጋሪውና ጠጅ አቅራቢው እና ዮሴፍ የፈርኦንን ህልም ፈታ።** | **የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ አቅርቡ**<br>**ማብራሪታ እና ማስረዳት፡**<br>1. ዮሴፍ ህልም አለመና በወንድሞቹ ተጠላ።<br>2. በያእቆብ ለእርሱ ያለውን ፍቅር የሚገልጽ ባለ ብዙ ቀለም ኮት ለዮሴፍ ተሰቶት ነበር ነገር ግን ይህ ከወንድሞቹ ዘንድ የበለጠ ጥላቻን አነሳሳ።<br>3. የዮሴፍ ህልም የሚያሳየው አስራ አንድ ወንድሞቹ፤ሊያ እና ከያእቆብ ጋር (ራሄል ሞታ ነበር) ወደፊት ለእርሱ እንደሚሰግዱለት የሚያሳይ ነበር።<br>4. የዮሴፍ ወንድሞች ተናደዱ እናም ሊገድሉት ተማከሩ ግን ለእስማኤላውያን (ለምድማውያን) ሸጡት።ሳያውቁት ለዮሴፍ የወደፊት ሹመቱ የእግዚአብሔርን እቅድ እየፈፀሙ ነበር።<br>5. ወንድሞቹ በጭካኔ የዮሴፍን በደም የተነከረ ኮት ዮሴፍ እንደሞተ ለሰበው ለያእቆብ መለሱለት እናም በጣም ለሚወደው ልጁ አለቀሰ።ያእቆብ "አታለዩ"' አሁን "የታለለው" ሆነ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አስረዱና ልጆቹ እንዲይዙት አበረታቱ።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።**<br>**አሳዩ: ስዕል - ህልመኛው ዮሴፍ።** |
| እዲታወስ | ተማሪዎች ራሳቸውን በዮሴፍ ቦታ አድርገው ለአባቱ ለያእቆብ ስለ አዲሱ ስራው ለመናገር ደብዳቤ እየፃፉ እንደሆነ እንዲያስቡ ጠይቁ ።ደብዳቤው ላይ ምን ሊጽፍ ይችላል? | ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይህንን ጥናት ከልሱ፡<br>**ሀ**. በህይወታቸው ምንም አይነት ሁኔታ ቢሆን በእግዚአብሔር ቁጥጥር ውስጥ መሆኑን ተማሪዎች እንደተረዱ አረጋግጡና እንዴት "ክፉን በክፉ" መመለስ እንደማያስፈልግ አስረዱ።<br>**ለ**. በጥናት አራት ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንደታገዙ እርግጠኛ ሁኑ። |
| የተግባር ሥራ | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ይህ ታሪክ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?<br>2. በእለት ተእለት ህይወታችሁ ታዛዥና ታማኝ ስለመሆን ምንድነው የተማራችሁት? በበረከት መንገድ ምን ትጠብቃላችሁ? | **ትምህርቱ እንዴት ነው ሚያነሳሳን?**<br>1. ***ኤፌሶን 4: 32*** በህይወት ውስጥ የሚመራ መርህ ስለመሆኑ ጠይቁ።<br>2. ጌታ ኢየሱስ መጥፎ ወይንም ጥሩ ናቸው ብሎ ለይቶ ስለማያይ እኛም እንደ ክርስቲያን ሁሉንም በመልካም አይን እኩል መመልከት ይኖርብናል።***(ማቴዎስ 5: 45)*** |

# የውጤት አሞላል ለአስተማሪው መመሪያ

## ደረጃ 3 ትምህርት:

- በዚህ ጥናት ጥያቄዎቹን ለመመለስ የግድ መጽሐፍ ቅዱስንን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል።
- ጥያቄዎቹ በተለያየ ይዘት ቀርበዋል የሰንጠረዥ ጨዋታ፣ ቃላት መፈልግና ዳሽ ሙላ።
- መመለስ ያለባቸው አዲሱ መደበኛ ትረርጉምንና መደበኛውን ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ በመጠቀም ነው።
- ጥያቄዎቹ በተቻለ አቅም የትኛውንም ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅመው እንዲመልሱ ተደርገው ነው የቀረቡት።
- ለሣምንቱ ትምህርት 20 ነጥብ የተመደበ ሲሆን ይህም በወሩ ውስጥ 80 ነጥብ ይሆናል።
- ደረጃ 3 በአብዛኛው እንደተገለጸው ለአንድ ጥያቄ አንድ ነጥብ ነው የሚሰጠው።

## ደረጃ 4 ትምህርት:

- ይሄኛው ከደረጃ 3 ጠንከር ያለ ጥናት ነው።
- የተወሰሰቡ ጥያቄዎችን መልስ ይፈልጋለል።
- ትምህርቱ በሙሉ ሲጠናቀቅና ጥያቄዎቹ ሙሉ መልስ ስመለሱ ለሣምንቱ ሃያ ነጥቦች ለወሩ ደግሞ 80 ነጥቦች ይያዛሉ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ውጤት አያያዝ

የውጤት አያያዝ ፍንጮች
በመጀመሪያ ተማሪዎቹ:

- እያንዳንዱን ትምህርት መርምረህ በማረም ትክክለኛ ለሆኑትና ላልሆኑት ምልክት አድረግ።
- በመመሪያው መሠረት አስፈላጊ ነጥቦችን ለማበረታቻ ሸልም።
- እያንዳንዱን ትክክለኛ መልስ የሚታረመው ሁል ጊዜ በተለየ ቀለም መሆን አለበት።
- ትክክለኛውን መልስ ምንም ነጥብ ባያስቆረጥም አስፈላጊ ሲሆን የቃላት ግድፈትን አርም።
- በከፊል ለተሠሩ መልሶች ነጥብ መቀነስ ያስፈልጋል።
- የወሩን አጠቃላይ መደመርና በገፁ መጨረሻ ባለው ቦታ ሙላ። ተማሪዎቹን ለማበረታታት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት ሁሉን ነገር መስራትና ደግ መሆን ያስፈልጋል። አስተማሪው በየወሩ ለተማሪዎቹ የቃል ማበረታቻ በትምህርቱ መጨረሻ በተሠጠው ባዶ ቦታ ላይ መሙላት ይጠቅማል። አስተያየቶች የሚሠጡት በጥሩ አቀባብ፤ ለጥራት፤ ለውጤት፤ ትምህርትን በመረዳት ደረጃ፤ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። አስተያየቶችን በተቻለ መጠን እንዲለያዩ እንሞክር።

ጥያቄዎች፤ ዐረፍተ ነገሮች፤ ግንዛቤዎች፤ ማበረታቻዎች፤ ወዘተ የሚደጋገሙ ከሆነ የተለያየ አይነት ጥያቄን ለመጠቀም ያገለግላሉ። ማሠላሠል ቢጠይቅም የተማሪዎቹን ፍላጎት ንቁ ማድረግ ያስፈልጋል። በየወሩ ተመሣሣይ ዓረፍተ ነገር ወይም ጥያቄ የሚደጋገም ከሆነ ትኩረት አይስብም።

**ደረጃ 3**

**ጠቅላላ አስተያየቶች:**
"ድንቅ ስራ ነው ጥያቄዎቹን በርግጥ በሚገባ አንብበሃቸዋል። በተለይ የመጨረሻውን መልስህን እጅግ ወድጄዋለሁ በተመረጡ ቃላት  ነው የጻፍከው።"
"ዮናታን ስለ ታታሪነትህ አመሰግንሃለሁ። ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርገሃለህ የረሳህውንም አንዱን ጽፌልሃለሁ።"

**መንፈሣዊ አስተያየቶች:**
"ሙሴ ከእስራኤል ልጆች አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥመውም እግዚአብሔር ከጎኑ ሆኖ አበርትቶታል"
"ዮሴፍ ከቤቱ ሩቅ በሆነ ሰዓት አባቱ እግዚአብሔርን እንዲወድ ያስተማረውን ትምህርት አልረሳም ነበር።"
"በርጠሚዎስ ወደ ጌታ ኢየሱስ ለመድረስ ቆርጦ ነበር፤ ኢየሱስ የተለየ እንደነበር ለመረዳት አለማየቱ ምንም ተጽዕኖ አላሳደረበትም።"

**ደረጃ 4**

**ጠቅላላ አስተያየቶች:**
"ሌላ አስደናቂ ውጤት! እንደተረዳሁት ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት አለሽ ደግሞም በጥናትሽ እንደተደሰትሽ አስባለሁ። አንዳንዱ በፍጥነት የሚታለፍ ቢሆንም እንኳ ጊዜ ወስደሽ በጥንቃቄ ስለሰራሽው አመሰግናለሁ። ጥረትሽን አደንቃለሁ።"
"በጣም ጥሩ ሞክረሻል ራሄል ከመልስሽ እንደተረዳሁት የታሪኩን ሃሳብ በደንብ አልተረዳሽውም ደግመሽ እንደምታነቢው ተስፋ አደርጋለሁ።"

**መንፈሣዊ አስተያየቶች:**
"ምሳሌዎች አንዳንድ ጊዜ ሰማያዊ ትርጉም የያዙ ምድራዊ ታሪኮች ወይም ከዛ የጠለቁ ይሆናሉ። በጥናት 3 ስላለው ምሳሌ የጠለቀ ትርጉም ምን ማሰብ ትችላህ?"
"እስጢፋኖስ እጅግ አሰቃቂ ሞት ነው የሞተው እንዲያ ሆኖ ለመሞት አልፈራም ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር አሁንም ሁሉን እንደሚቆጣጠርና ቢሞትም ከጌታ ከኢየሱስ ጋር እንደሚሆን ያምን ስለነበር ነው።"

©Bible Educational Services 2015

www.besweb.com

Registered Charity UK 1096157